ከመጋቢ፡ በዳኩ፡ ስጦታ፡
ለመጋቢ፡ [illegible]፡ mar.1999

# በእግዚአብሔር ምሪት የሚሰጥ አገልግሎት

በመጋቢ አበራ ተሰማ

1990 ዓ.ም ታተመ
1998 እ.ኤ.አ

አርታኢ ወንጌላዊ ሙሉ ወርቅ መኩሪያ

በፓስተር አበራ የተዘጋጀውን ፅሁፍ የእግዚአብሔርን አመራር በሕይወታቸው፣ በኑሮአቸውና በአገልግሎታቸው ለሚሹ ሁሉ ቀለል ባለ መንገድ የእግዚአብሔርን ምሪት እንዲረዱ የሚረዳቸው መመሪያ ሆኖ ሊጠቅማቸው የሚችል ጠቃሚ መሣሪያ ነው፡፡ የእግዚአብሔር በየዘመኑ የልቡን ሀሳብ ለማገልገል የሚናፍቁና እንደ ቃሉ በውሳኔ ራሳቸውን የሰጡን የእርሱን እውነት ለራሳቸው ለመፈለግ፣ ለመታዘዝና ለሌሎችም በቃሉና በኑሮ ምስክር የሚሆኑለት አገልጋዮችን ይፈልጋል ፓስተር አበራ ከእነዚህ አገልጋዮች መካከል አንዱ ስለሆነ እግዚአብሔር አምላኬን በሙሉ ልቤ አመሰግናለሁኝ፡፡ ዕዝ 7፤10

ቄስ ምትኩ ዘለቀ

*የመካኒሣ መካነ ኢየሱስ ቄስ*

መጋቢ አበራ ተሰማ "በእግዚአብሔር ምሪት የሚሰጥ አገልግሎት" ብለው የፃፉትን መጽሐፍ ተመልክቸዋለሁ፡፡ በተለይ በአስተዋፅዖ መልክ መቅረቡ ለቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለቤተሰብ ፀሎት፣ ለሰንበት ት/ቤትና፣ ለመ/ቅ/ት/ቤት የሚሰጠው ጠቀሜታ ቀላል አይሆንም፡፡

ወንጌላዊ ሺፈራው ፈይሳ

*ጌኛ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን*

ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ
ማባዛት ወይም መልሶ ማተም
የተከለከለ ነው

Copy right Abera Tessema, August 1998
All Rights Reserved

*Address:-*
PASTOR ABERA TESSEMA
Amanuel Evangilical Ethiopian Church
P.O.Box 5254
Takoma Park, Mary Land 20912
U.S.A.

## ምስጋና

እንደ ቃሉ በእግዚአብሔር መንፈስ በመመራት ለማገልገል ለሚዘጋጁ ሁሉ የሚሆን ይህን ጥናታዊ የሆነ ትምህርት እንድፅፍ ልቤንና መንፈሴን ያነሳሳውን ከሀጢያቴ አድኖ እንዳገለግለው ፀጋውን ለሰጠኝ ለአምላኬ ክብርና ምስጋናን እሰጣለሁ፤ እንደዚሁም ደግሞ በአጠገቤ በመቆም የውሳኔና የቆራጥነትን ሕይወት በመኖር ስታበረታታኝ ለነበረችው ውድ ሚስቴ ሣራ ባህታ ጌታ ስለ ሰጣት ፀጋ አምላኬን አመሰግናለሁ እንደዚሁም ከእኛ ስለተገኘው መፅናኛ ስለሆነኝ ስለልጃችን ሳሙኤል አበራ ጌታን ከልቤ ላመሰግነው እወዳለሁ እንዲሁም በአገልግሎቴ በፀሎትና በሀሳብ አብረውኝ ለቆሙት ወገኖቼ ሁሉ ስለ እነርሱም እግዚአብሔር አምላኬን አመሰግናለሁ። ይህን ፅሁፍ በማርቀቅና በመፃፍ የምዕራፉንም ቅደም ተከተል መልክ በመስጠት የተባበሩኝን ወንድሜ መንገሻ ወንዴን፣ ዶ/ር ዘላለም እሸቴንና አለማየሁ ሰይፍን አመሰግናለሁ።

ወንጌላዊ ሙሉ ወርቅ መኩሪያ ዋናውን ፁሁፍ በማረምና ቋንቋውንም በማግራት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓልና አመሰግነዋለሁኝ በዚህ ቦታ ያልጠቀስኳቸው በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለዚህ ፁሁፍ መሳካት በተለያየ መንገድ አስተዋጽኦ
ስላደረጉት ወገኖቼ እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ በሁሉ አምላኬ ይባርካቸው እላለሁኝ። አሜን !

*መጋቢ አበራ ተሰማ*

# መቅድም

እግዚአብሔር ሰውን ሊመራው ፈጠረው፡፡ ለዚህም ሰው ከተፈጠረበት ዕለት ጀምሮ ለኑሮው የሚሆን መመሪያና ትዕዛዝ ተሰጠው ይህንንም ሊያደርግ የሚቻልበት የራሱ ፈቃድ ያለውም አድርጎ ፈጠረው፡፡

እግዚአብሔር ሰውን ብቻ ሳይሆን ከሰው በፊት ተፈጥረው ለነበሩ ሁሉ የሚመሩበትን የራሳቸው የሆነ መመሪያ ሰጣቸው ከእርሱ ፈቃድ እንዳይወጡ ይህን ያላደረጉ በተሰጣቸው ትዕዛዝና መመሪያ ያልተመሩ ከፈቃዱ ወጡ፡፡

ሰውም ሆነ ሌላው ፍጡር ሁሉ ያለ እግዚአብሔር በራሱ ሀይልና መመሪያ ሕይወቱን በትክክለኛ መንገድ ሊመራ አይችልም እኒህ ፍጡራን ሁሉ የሕይወትንና የኑሮን ጣዕም ተገንዝበው በሰላም ሊኖሩ የሚችሉት በተሰጣቸው መለኮታዊ ምሪት ዛሬም በዚህ ዓለም ነገም ከዚህ ዓለም ውጪ የበላይ እግዚአብሔር መሆኑን ከወዲሁ ሲያውቁ ነው፡፡ “ሁሉ ከእርሱ በእርሱ ለእርሱም ነውና ...” ተብሎ በሮሜ 11:36 እንደተመሰከረው፡፡

ትላንትም፣ ዛሬም ይሁን ነገ ሥርዓት ባለው ሁኔታ ፍጡር ሁሉ እንዲመራ የውስጥ እና የውጪ መመሪያዎች ተሰጥተውታል በተለይ ከፍጡር ክቡር የሆነው “ሰው” በተጨማሪ የተሰጠው ብዙ መመሪያዎች አሉት አንደኛው “ቃሉ” መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ በተለይም እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ትክክለኛ በተድበሰበሰና በተመሳሳለ ሁኔታ እንዳንኖር ይረዳን ዘንድ ሁል ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ጋር አድርገን ልንጠቀምበት የምንችል መሠረታዊ እውነቶችን በማካተት ቃሉን መሠረት በማድረግ ወጥ የሆነ ጥናታዊ ፁሁፍ ለአንባቢያን ቀርቧል እንደተፃፈው በመለኮታዊ ምሪት በመመራት መሪያችንንም ተከትለን ማገልገል እንድንችል እግዚአብሔር አሁንም ሁላችንን ይምራን፡፡ አሚን!!

*ወንጌላዊ ሙሉ ወርቅ መኩሪያ*

## መክሥተ አርእስት /Table of Content/

ገፅ

መቅድም ------------------------------------------------------ --IX

ክፍል 1 የመለኮታዊ ምሪት አስፈላጊነት

ምዕራፍ አንድ የእግዚአብሔር አመራር

1.ሥርዓተ ምሪትን የሰጠ እግዚአብሔር ነው--21-23

2.እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው ትዕዛዝ ምሪት-- 23-24

3. በእግዚአብሔር የሚመሩ ሰዎች መለያቸው የውሳኔ ኑሮአቸው ነው---------------------24-25

ምዕራፍ ሁለት የአመራር መነሻና ሂደት

1. ለምን አመራር አስፈለገ ?----------------27-28

2. አመራር ከግል ሕይወታችንና ከቤታችን ይጀምራል---------------------------------28

3. መሪ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው ?---29-30

ምዕራፍ ሦስት አመራር የማይግና የመሻሻል ባህሪይ አለው

1. መሪዎችን የምንታዘዘው ለምንድ ነው ?--31-32

2. የመሪው ጥሪው አገልግሎቱ------------ 32-33

ምዕራፍ አራት የመሪ መለያ

1. የመልካም መሪ ባሕሪያት------------------35

2. ትክክለኛ ያልሆነ መሪ ምን ይመስላል-----36

3. የእውነተኛ መሪ መስፈርቶች-------------36-38

ክፍል 2 የቃሉ መረዳት አስፈላጊነት

ምዕራፍ አምስት፡ የቃሉ መለኮታዊ ሥልጣኑና ሀይሉ

1. ክርስቲያን አገልጋይ ቃሉን ለምን ያውቃል ?--42
2. የእግዚአብሔር ቃል ምን ዓይነት ተግባራትን በሕይወታችን ያደርጋል--------------------43
3. የእግዚአብሔር ቃል በምን ተመስሏል?----43
4. የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅና ለመረዳት የሚረዱ መሰረታዊ መስፈርቶች-------44

ምዕራፍ ስድስት፡ የቃሉ እውነት የተረጋገጠው በመፈፀሙ ነው

1. ስለ ኢየሱስ በተነገረው የትንቢት ቃል-45-46

ምዕራፍ ሰባት የእግዚአብሔር የመለኮት አንድነት

1. የእግዚአብሔር አብ ለወልድ የሰጠው የበላይነት---------------------------47
2. የእግዚአብሔር ወልድ ፍፁም ሰውነቱና አምላክነቱ-----------------------------47-48
3.እግዚአብሔር ወልድ ለቤተክርስቲያን ምን ሰጠ?-------------------------------48
4.እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምን ሰጠ?-49-50

ምዕራፍ ስምንት እግዚብሔር መንፈስ ቅዱስ

1. መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ዓለም ውስጥ-----51
2. ሕያው የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች----52
3. የእግዚአብሔርነት ባህሪው-------------------52



4. ሕያውነቱን የሚገልጡ አስረጂዎች----------53
5. መንፈስ ቅዱስ ለማን ይሰጣል-------------53-54
6. መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎታችን ጥቅም/ፍሬ/ይሰጣል-----------------------54-55
7.መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት **56-57**
8.መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ-57-58

ክፍል 3 አገልግሎት

ምዕራፍ ዘጠኝ የክርስቶስ አገልግሎት

1. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሀዋርያ--------------61
2. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ነብይ---------------62
3. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ወንጌላዊ------------66
4. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መጋቢ /እረኛ/----63
5. እየሱስ ክርስቶስ እንደ አስተማሪ----------63-64

ምዕራፍ አሥር፡ የሀዋርያት አገልግሎት

1. የሀዋርያነት አገልግሎትና ሥልጣን--------65-66
2. የነብይነት አገልግሎት ስጦታ-------------66-67
3. የወንጌላዊነት ስጦታ----------------------67-68
4. የመጋቢነት /እረኛ/ አገልግሎት ስጦታ--68-69
5.የአስተማሪነት አገልግሎት ስጦታ-----------69-70

ምዕራፍ አሥራ አንደ፡ የአገልግሎት ስጦታዎች ሥራ

1. ስም ትርጉምና ዓላማ----------------------71-72
2. የሽማግሌዎች አገልግሎት-----------------72-74
3. የዲያቆናት አገልግሎት--------------------74-75

ምዕራፍ አሥራ ሁለት፡ የተሳሳቱ አገልግሎቶች በአገልግሎት ስጦታዎች ስም
1. የሐሰተኞች ሀዋርያት አገልግሎት----77-78
2. የሐሰተኞች ነቢያት አገልግሎት-------78-79
3. የሐሰተኞች ወንጌላውያን አገልግሎት---79
4. የሐሰተኞች መጋቢዎች /እረኞች/ አገልግሎት----------------------------80
5. የሐሰተኞች አስተማሪዎች አገልግሎት---81



## ክፍል 4 ምክሮች

ምዕራፍ አሥራ ሦስት ለአገልጋይና ለአገልግሎቱ ጠቃሚ ምክሮች
1.የፀሎት ጊዜ ለአገልጋይ የሚሰጠው ጥቅም-85-86
2. ከእግዚአብሔር ራዕይ መቀበል ማግኘት አስፈላጊነቱ--------------------------------86
3. ራዕይ እንዴት እንቀበላለን-----------------87
4. ከእግዚአብሔር የሆነ ራዕይ የሚከተሉትን ይመስላል--------------------------------88
5. ከእግዚአብሔር የተሰጠን ራዕይ ሊጠፋ የሚችለው እንዴት ነው?---------------88
6. ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ራዕይ እንዴት እንለየዋለን--------------------------------89
7. እግዚአብሔር ቤቱን እንዴት በአገልጋዩ እንደሚሠራ እንወቅ---------------------89-90

አበርክቶት፡-

በእግዚአብሔር መንግሥት
ከክርስቶስ ጋር ላለ ች ሚስቴ ሣራ ባሀታ
መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በፍቅር አበረክታለሁ፡፡

# ክፍል 1

## የመሪኮታዊ ምሪት አስፈላጊነት

### ምዕራፍ አንድ የእግዚአብሔር አመራር

1. ሥርዓተ ምሪትን የሰጠ እግዚአብሔር ነው
2. እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው ትዕዛዝ ምሪት
3. በእግዚአብሔር የሚመሩ ሰዎች መለያቸው የውሳኔ ኑሮአቸው ነው

### ምዕራፍ ሁለት የአመራር መነሻና ሂደት

1. ለምን አመራር አስፈለገ
2. አመራር ከግል ሕይወታችን ከቤታችን ይጀምራል
3. መሪ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው ?

### ምዕራፍ ሦስት አመራር የሚደግና የመሻሻል ባህሪይ

1. መሪዎችን የምንታዘዘው ለምንድ ነው ?
2. የመሪው ጥሪውና አገልግሎቱ

### ምዕራፍ አራት የመሪ መለያ

1. የመልካም መሪ ባሕሪያት
2. ትክክለኛ ያልሆነ መሪ ምን ይመስላል
3. የእውነተኛ መሪ መስፈርቶች

## ምዕራፍ አንድ
## የእግዚአብሔር አመራር

ስለ አመራር በመጀመሪያ ሥርዓት የሰጠና የጀመረ እግዚአብሔር ነው ለተለያዩ ፍጥረታት ማለትም ለመላእክት፣ ለሰው ልጆች፣ ለእንሰሶች… ወዘተ የተለያዩ ሥርዓተ አመራሮችን እንደሰጣቸው ከጌታ ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁም የእግዚአብሔር ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ ተምረው ከፃፉትና ከተናገሩት ነገሮች ብዙ ስለ አመራር እንገነዘባለን፡፡ ይህም ቃሉ የሚደግፈው ነው፡፡

ያለ እግዚአብሔር አመራር እውነተኛ ምሪትና ራዕይ የለም በተለይም መንፈሳዊ ሥራ ያለ መንፈስ ቅዱስ ምሪት አለመሥራት መቻል ብቻ ሳይሆን ያለ ራዕይ /ዓላማ/ መሆንን ያመጣል ራዕይ ያጣ መንፈሳዊ አገልጋይ መረን ይወጣል መረን የወጣ ከእግዚአብሔር አመራር በመውጣቱ ከእግዚአብሔር ፈቃድ እና ሀሳብ ውጪ የሆነ ኑሮን ይኖራል፡፡ ይሄ እንዳይሆን ራዕይ ያለው ሎሌ መሪ /Servant leadership/ ምን መምሰል እንዳለበት ማወቅና መረዳት የሚቻለው በእግዚአብሔር ሲመራ ብቻ እንደሆነ ቃሉን መሠረት በማድረግ እንመለከታለን፡፡

### 1. ሥርዓተ ምሪትን የሰጠ እግዚአብሔር ነው

1.1 እግዚአብሔር የፈጠራቸው ሕያዋንና ግዑዛን የሆኑ ነገሮች ሁሉ አስቀድመው በእግዚአብሔር ፈቃድና ምሪት

የተፈጠሩ ብቻ ሳይሆን በምሪቱም ትዕዛዝ ዛሬም ቢሆኑ የሚመሩና የሚኖሩ ናቸው።

ኤር 10፡10-16

1.2 ከእግዚአበሔር ፍጥረታት አስገራሚና ድንቅ ተብለው ከሚጠሩት መካከል አንደኛው የመላእክቶች አፈጣጠርና አኗኗር ነው እኒህ መላእክት ፈጣሪያቸው እንዳዘዛቸው የሚኖሩ የሚያደርጉም ናቸው ከአመራሩ ውጪ በመሆን መልዕክትን አይናገሩም።

ዳን 9፡21-23 ሉቃስ 1፡26-38

1፡3 ከመላእክት ጋር በሕብረት አገልግሉት የሚመደቡ ሱራፍኤልና ኪሩቤል በእግዚአብሔር ዙሪያ ቅድስናውንና ብዕሕናውን በመጠበቅ ታላቅነቱን እየተመለከቱ በአክብሮትና በስግደት የሚያመልኩት በክብሩ ዙፋን ዙሪያ ያሉት እኒህ መላአክቶች ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ ሁሉ ጊዜ እንዲያመልኩት የታዘዙት ናቸው ይህንንም ዕለታዊ ተግባራቸውን በማድረግ ያለማቋረጥ እንደተደነገገላቸው ያደርጉታል ለሥርዓቱም ተገዝተው ይኖራሉ።

ዘፍ 3፡24 ኢሳ. 6፡2-3 ሕዝቅ 10፡1-5 ዕብ 1፡6 ራዕይ 4፡8

1.4 እኒህ በእግዚአብሔር የተመረጡ መላእክት በእርሱ ሥርዓተ ምሪት ውስጥ መኖራቸውን ሲናገር የተመረጡት መለአክት ብሎ ይጠራቸዋል።

1ጢሞ 5፡21



1.5 ልንቆጥራቸውና ልንገምታቸው የማንችል አእላፋት ጊዜ አእላፍት የሆኑ ናቸው ምንም እንኳ ከግምትና ቁጥር በላይ ቢሆኑም በሥርዓቱ ውስጥ ኃላፊነታቸውንና ተግባራቸውን ያለማቋረጥ ያከናውናሉ።

ዕብራ 12፡22-24 ራዕይ 5፡11

2. <u>እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው ትዕዛዝ ምሪት</u>

2.1 እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከፈጠራቸው በኋላ ያዘዛቸውን እንዲያ እንዲያደርጉት የሰጣቸው ምሪት ዘፍ 1፡26-28 2፡16-17

2.2 እግዚአብሔር የሚቀበለውን ዓይነት መስዋዕት አቤል ከዚህ በፊት እንደተሰጠው ትዕዛዝ በምሪት አቀረበ ዘፍ 4፡ 3-4

2.3 እግዚአብሔር ሄኖክ በዘመኑ ሁሉ ከእርሱ ጋር እንዲጓዝና እንዲኖር መራው ዘፍ 5፡ 21-22

2.4 እግዚአብሔር ኖኅ መርከብን እንዲሰራ ራዕይን ሰጠው እንደተሰጠውም ትዕዛዝ ሰራ የቃል ኪዳን ምሪትም ተሰጠው ዘፍ 6፡13-18

2.5 እግዚአብሔር አብርሃም ጣኦት ከሚያመልከበት ሕዝብ ተለይቶ እርሱ ወደሚመራው ምድር ተለይቶ እንዲወጣ ትዕዛዝ ምሪትን ሰጠው

ዘፍ 12፡1-4

2.6 እግዚአብሔር ይሥሀቅን ወደ ሌላ አገር አትሂድ እኔ እዚሁ ምድር እያለሀ እባርክሀለሁ ሲል መራውና አዘዘው ዘፍ 26፡1-4 ዘፍ 26፡12

2.7 እግዚአብሔር ለያዕቆብ ገና በእናቱ ማህፀን ሣለ የሚሆነውን ምሪትና ትዕዛዝ ሰጠው
ዘፍ 25:23 28:10-17 35:1

2.8 እግዚአብሔር በዮሴፍና በቤተሰቦቹ ሕይወት የሚሆነውን ራዕይ አስቀድሞ ሰጠው ዘፍ 37:5-11 45:1-8

2.9 እግዚአብሔር ለሙሴ እሥራኤል ሊያደርግ የሚገባውን ምሪትና ትዕዛዝ ሰጠው ዘፀ 3:6-12

2.10 እግዚአብሔር አምላክ ኢያሱ ሊያደርገው የሚገባውን ምሪትና ትዕዛዝ አስቀድሞ ነገረው
ኢያሱ 1:9

2.11 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱና ለደቀመዛሙርቱ ሊያደርጉትና ሊጠብቁት ሊከተሉትም የሚገባቸውን ትዕ ዛዝ ሰጣቸው
ሉቃስ 24 45-49 የሐዋ 1:8

2.12 እግዚአብሔር ለሐዋርያው ጳውሎስ የሰጠው ምሪትና ራዕ ይ በዘመኑ ሁሉ በመከራው ውስጥ ሁሉ እንዲያደርግ አዘዘው፡፡
የሐዋ 9:8 የሐዋ 26 17-20 ገላ 1:15-17

3. <u>በእግዚአብሔር የሚመሩ ሰዎች መለያቸው የውሳኔ ኑሮአቸው ነው</u>

3.1 የእግዚአብሔር ምሪት በጊዜ መርዘም ተገድቦ የሚቀር እንዳልሆነ በማወቅ የሚጠበቅባቸውን ያደርጋሉ ዘፍ 6:13-18 7:13-16



3.2 እግዚአብሔር እንዳለውና እንደተናገረው ለመመራት የሕይወታቸው መመሪያ መሆኑን አውቀው ይኖራሉ
ዘፀ 32: 21-24 ኢያሱ 24:19-24

3.3 እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ምሪት ሲከተሉ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ወደ ኋላ አይሉም ይህም ሊገድባቸው አይችልም
ዘፍ 39:7-23 1ሳሙ 17:45-49 2 ዜና 18:13 ዳን 3:13-18 5:16-17 6:19-28 የሐዋ 7:54-60 2ጢሞ 4: 6-8

# ምዕራፍ ሁለት

## የአመራር መነሻና ሂደት

ስለ አመራር ስናስብና ስንጠይቅ እውነተኛውን ነገር ለማስተማር እና ለማስጨበጥ አመራር የት እና መቼ እንደተጀመረ አስቀድሞ ማወቅና መረዳት ተገቢ ነው እንግዲህ አመራር የት ተጀመረ ለሚለው ጥያቄ አመራር የተጀመረው ከሰማይ ሲሆን የመጀመሪያው መሪና ስርዓት ሰጭ ደግሞ እግዚአብሔር አምላካችን እንደሆነ የታመንና የታወቅ ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ለመላእክቱም ሆነ ለፍጥረቱ እርሱ በሰጠው ስርዓትና ትዕዛዝ መሰረት ይወጡና ይገቡ እንደነበር የእግዚአብሔር ቃል በግልፅ ያስተምረናል መዝ (148) ፡ 1-5, መዝ (103)፡ 17-22,

ከዚሁ ጋር አብረን መመልከት የሚገባን ነገር መታዘዝ በሰማይ እንደተጀመረ አመፅም በሰማይ እንደተጀመረ ቃሉ ይነግረናል፡፡ ይሕም አመፅ ሉሲፈር የተባለው የወደቀው መላእክ በትዕቢቱና ክርኩሰት ተባባሪዎቹ ጋር እንደተጣሉ የእግዚአብሔር የአምላካችን ቃል ይነግረናል ኢሣ 14፡12-16, ሕዝ 28፡ 16-19, 2ጴጥ 2፡4, ራዕይ 20-10

1. <u>ለምን አመራር አስፈለገ ?</u>

1.1 እግዚአብሔር መሪና የስርዓት አምላክ ስለሆነ ነው፡፡ ኢሣ 33-22, ቆሮ 14፡32-33

1.2 ሰላም እንዲሰፍን የሰላም አምላክ ስለሆነ መሣፍ 6፡24, 1ቆሮ 14፡33, ዮኀንስ 14፡27

1.3 የእግዚአብሔርን አመራርና ትምሕርት ለማግኘት መዝ 32 8, ኢሣ 52፡10-13, ኢሣ 42፡16

1..4 የሚመራንና የሚገልፅልን አምላክ እንዳለን የማያውቁ እንዲያውቁ ለማድረግ ዳን2 27-30 ዘፍ41፡16 ዮሐን16፡13

1.5 ተልኮአችንን እንድንወጣ መነሻና መድረሻችንን እንድንረዳ ነው፡፡ ዮሐን 4፡34 ዮሐን ፻7፡4-5

1.6 ፍሬ ለማየትና ውጤታማ ለመሆን ዮሐን 15፡8

1.7 መልካሙን ምሪት ተከትሎ እሩጫ መጨረስ እንዲቻል፡፡ 2ጢሞ 4፡7-8, ዮሐን17-4

## 2. <u>አመራር ከግል ሕይወታችንና ከቤታችን ይጀምራል</u>

አመራር ከግል ሕይወታችን ጀምሮ በኑሮአችንና በሥራችን ወይም በአገልግሎታችን ያስፈልገናል ለእዚህም ነው ኢያሱ እኔና ቤቴ ሲል ኢሣያስ ደግሞ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች ይላል፡፡ በጢሞቲዎስ ላይ ቤቱን በመልካም የማይመራና የማያስተዳድር ሰው እንዴት የእግዚአብሔርን ቤት ሊመራና ሊያስተዳድር ይችላል ይለናል፡፡ ኢያሱ 24፡15, ኢሣ 8፡18 1ጢሞ 3፡5 ስለዚህ አመራርና አስተዳደር ከግለሰብ ሕይወት ጀምሮ ወደ ቤተሰብ ከዚያም ወደ ሕዝብ መንግስት ድረስ የሚዘልቅ መሆኑን ማወቅ ይገባል፡፡ ክርስቲያን መንፈሣዊ ሕይወቱን ከማሳደግ ጀምሮ በኑሮውና በአገልግሎቱ ፍሬ እስከ ማሣየት ድረስ ለጤናማ እድገት መልካም ምሣሌነትም ያስፈልገዋል፡፡ በኑሮውም ሆነ በተሰጠው በማንኛውም አገልግሎት አመራርን ካለወቀና ካልተረዳ እግዚአብሔር በሕይወቱ ለመስራት ያስቸግረዋል፡፡ ቢሠራም እንኳ ማስተዋል ስለማይችል የተጨበጠ ፍሬን ለማየትና ለማጨድ አይችልም፡፡



## 3. <u>መሪ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው ?</u>

ለዚህ ጥያቄ መልስ መሪነት በሁለት ነገሮች የሚገኝ ነገር ሲሆን እነርሱም

1. በተፈጥሮ 2. በመማር ልናገኛቸው እንችላለን

እግዚአብሔር አምላክ አንዳንዶቹ በተፈጥሮአቸው የመሪነትና የአስተዳደር ስጦታ በተፈጥሮ ስለተሰጣቸው ብዙዎች ሲቀበሏቸውና ሲታዘዙላቸውም እናያለን ይህ ጥልቅ ሚስጥሩ ለእግዚአብሔር ነው፡፡ ዘፍ 1፡28, ዘፍ 25፡22-23 ስለአመራር ስናስብ ሰዎች ሁሉ መሪነት በተፈጥሮ ሊኖራቸው ላይኖራቸውም ቢችል መሪነት በመማር ልናዳብረው የምንችል እንደሆነ ግን ሁሉም ሰው ሊቀበለው የሚገባ እውነት ነው፡፡ ለዚሕም ነው ያስተምራቸው ዘንድ መንፈሱን የሰጣቸው ልጆችሽ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ የሚለው ቅዱስ ቃሉ እውሮችን በማያውቁት መንገዱ ይመራቸዋል ይላል፡፡ ኢሣ 42፡16 ኢሣ 54፡13 ነህ 9፡12-15 እንግዲሕ ይሕን ካልን የመሪነት ባሕሪ የሚያድግና የሚቀጥል እንጅ አንድ ጊዜ መሪነትን ተቀብያለሁ ወይም በተፈጥሮዬ የመሪነት ስጦታ አለኝ ተብሎ መዘናጋቱ ሊማርና ሊያዳብር ያለውን መሪነቱን ሊያጣና የሚማራቸውን ብዙ ነገሮች ሳይማር ሊቀር እንደሚችል መረዳት ይኖርበታል የተፈጥሮ መሪነት ያላቸው ቢሆኑም እንኳ ቢሰለጥኑ ይበልጥ ከሌሎችም የሚማሩት እንዳለ ሊያውቁት ያስፈልጋል 2 ጢም 3፡14-17, ዮሐን 13፡12-17

መሪ አገልጋይ ማለት መሪ ብቻ ሳይሆን ተማሪም ነው ከእግዚአብሔር ከአምላካችን በስተቀር ፍፁም መሪ የለም አንድ መሪ ይህን ማወቁ የሚጠቅም እንደሆነ ማሰብ ያስፈልጋል።



## ምዕራፍ ሦስት

## አመራር የማደግና የመሻሻል ባህሪይ አለው።

የእግዚአብሔር ቃል እንዲሕ በማለት ይነግረናል ጅማሬህ ትንሽ ቢሆንም ፍፃሜህ ግን ታላቅ ነው ይላል። በትንሹ ታማኞች ስንሆን እግዚአብሔር ለብዙ ነገር ይሾመናል በትንሹ ካልታመንን ግን ለብዙ ነገር እንድንሾም ብቁ አይደለንም ማለት ነው። ጳውሎስ ታማኝ አድርጎ ስለቆጠረኝ ለአገልግሎት ሾመኝ ሀይል የሰጠኝን ጌታችን እየሱስ ክርስቶስን አከብረዋለሁ ይላል 1ጢሞ 1-12, ማቴ25:2 3,

ታላላቅ መሪዎች ሆነው በምሣሌነት የሚጠቀሱ ሰዎች በጊዜያቸው ምሪትን ተቀብለው እግዚአብሔር በላያቸው ላስቀመጣቸው መሪዎች በመታዘዝ የሚገኘውን በረከት ያውቁ ነበሩ። በዚህም ምክንያት በሕይወታችውና በአመራር አድገዋል ዛሬም በመሪነት እስከመጨረሻ ለመዝለቅ ለሌላውም በረከት ሆነን ለማድግ እያንዳንዳችን እግዚአብሔር ከእኛ በላይ ላስቀመጣቸው መሪዎች ሁሉ መታዘዝ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን ትልቅ የመሪነት ቦታ እንድንደርስ የሚያደርገንና ወደተለየ በረከት ውስጥ እንድንገባ የሚያደርገን ብቻ ሳይሆን በአመራር እንድናድግ የመሪነት እውነተኛ ባህሪዎች ከሆኑት መሰረቶች አንዱና ዋነኛው ነው።

1. መሪዎችን የምንታዘዘው ለምንድን ነው ?

1.1 ባለስልጣኖች ሁሉ በእግዚአብሔር ስለተሾሙ ሮሚ 13:1-2

1.2 የእግዚአብሔርን ጊዜ ለመጠበቅ እንድንችል መክ 3:11, ገላ 4:4

1.3 በጊዜው ከፍ እንዲያደርገን 1ጴ 5:6, ፊል 2:6-11

1.4 መታዘዝ ማትረፍ ስለሆነ። ዘፍ 7:13-17

1.5 አምላካችን ተስፋውን በዚህ ሁኔታ ስለሚፈፅመው ኢያሱ 21:43-45

## 2. <u>የመሪ ጥሪውና አገልግሎቱ</u>

2.1 በእግዚአብሔር የተጠራ ነው ዘፅ 3:6-12, የሐዋ 13:2-4

2.2 የጠራውን እግዚአብሔርን ያውቃል ዘፍ 12:1-4, 15 6 ዮሐን 8:54-55, 2ጢሞ 1:12

2.3 ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትና ወዳጅነት አለው 1ዮሐ 1 3, ዘፍ 15:6, ያዕ 2:23

2.4 የጠራውን እግዚአብሔርን መምሰልና ማምለክ ይወዳለ 1ጢሞ 4:8, ኢያሱ 24:15

2.5. እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳለበት ያውቃል የሐዋ 5:29, ገላ1:15-16, ዘፍ 6:22

2.6. እግዚአብሔርን እየጠየቀ ይሰግራል ይመራሉ። 1ሣሙ 23:1-5, የሐዋ 16:9-10

2.7 እግዚአብሔር በሚሰራው ይደሰታሉ መዝ 27:4, ሉቃ 10:17,የሐዋ, 13:48

2.8 የእግዚአብሔር ጽድቅና አዳኝነት ያሳያል። ዘፍ 6:9, 2ጢሞ 4:17 አስቴር 4:16

2.9 ራእይ የሰጠውን ጌታ ይታመናል ዘፍ 41:16, ዳን 5:17, የሐዋ 27:25



2.10 የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከባርነት ያወጣል ዘፅ 3:6-12, የሐዋ 3:19-21

2.11 በእግዚአብሔር ታምና በመከራ ውስጥ ሁሉ ይፀናል ዘፍ 45-1-8, 2ጢሞ 1:12

2.12 የእግዚአብሔርን ታላቅነት ያውቃል 1ሣሙ 17-45-48, 2ዜና 34:1-7

2.13 የእግዚአብሔርን መለከታዊ ሚስጥር ይገልፃል ኤፌ 3:1-9, ዳን 2:22-30

# ምዕራፍ አራት

## የመሪ መለያ

በመሪነት ውስጥ የሚታዩ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም ትድሚያ ከሚሰጣቸው ነገሮች መካከል ዋነኛውና አስፈላጊው ነገር የመሪው ባህሪያት ናቸው መልካሙንና ትክክለኛ ያልሆኑትን ባህሪዎችን በመመልከት እውነተኛ መሪዎችን እንዴት እንደምናገኝ የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመለከታለን፡፡

### የመልካም መሪ ባሕሪያት

1.1 በእግዚአብሔር ይታመናል ቃሉንም ያምናል፡፡ ዘፍ 12፡1-4, ኢሣ 26,3-4

1.2 ነፃነትን ይሰጣል ያምናል ማቴ 10፡7-8, ገላ 5፡1

1.3 የሚያደርገውን ያውቃል ነህ 6፡12, 2ቆር 8፡21-24

1.4 ከበታቹ ያሉት ጠቃሚዎች እንደሆኑ ያውቃል ያሳውቃልም ሉቃ 6፡12-13 ፊል 2፡20-24 1ጴጥ 5፡13 ዘዳ 3፡7-8 2ጢሞ 2፡1-2

1.5 ከበታቹ ያሉትን ያዳፍራል ያበረታታል ዘዳ 31፡ 7-8, 1ጤሞ 4፡11-16, 1ጴጥ 5፡9፡11, 3ኛ ዮሐን 1-4, ዮሐን 21 ፡ 15-17

1.6 ሐሣቡን የማስተላልፍ ችሎታ አለው፡፡ 2ኛ ቆር 8፡23, 1ጴጥ 5፡13, የሐዋ 9፡27-29

1.7 የቱ መቅደም እንዳለበት ያውቃል ፡፡ 1ዜና 28፡9

1.8 ሊሰሩ የሚችሉትን ያውቃል ለይቶም ያስተምራል ያሰለጥናል ቀደም ብሎ ዘላቂውን ያውቃል ሉቃ 6፡12-13 10, 1-3, 2ጤሞ 2፡1-3 ኤር 29 ፡ 11-13, 1ኛ ዜና 29፡1, የሐዋ 1፡8 2ኛ ጤሞ 2፡2-3,

## 2. ትክክለኛ ያልሆነ መሪ ምን ይመስላል ?

2.1 የሚያስበውን ሁሉ ራዕይ ለማድረግ ያስባል፡፡ የጠራ ራዕይ የለውም መሣፍ 21፡25, 1ኛ ሣሙ 15-13-23

2.2 በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ በራሱ የሚታመን በፍርሐት የተሞላ ነው 1ኛ ሣሙ 17፡11

2.3 የሚያወላውል ሐሳብ ያለው ነው ያዕቆ 1፡7-8, ራዕይ 3፡15-16

2.4 ወዳጅና ጠላቱን የማይለይ ነው 1ሣሙ 18፡28-29

2.5 ሕዝቡን ያለ ራዕይ በመምራት መረን ልቅና ስርዓት የለሽ የሚያደርግ ነው፡፡ ምሳሌ 29፡18

2.6 እግዚአብሔር በማይከብርበት ነገር እግዚአብሔርን ከሕዝቡ ጋር በመሆን ያስቆጣል ዘፀ 32፡1-6

2.7 ዓለማዊና ሥጋዊ በሆኑ ነገሮቹ ይወሰዳል መሣፍ 16፡16-20, 1ኛ ጢሞ 6፡10

2.8 በሐይልና በማስፈራራት ዕድሜአቸውን ሊያረዝሙ ይፈልጋሉ ከሥነ ምግባር ውጪ የሆኑትን ነገሮች በግልፅ በመዳፈር ያከናውናሉ የሐዋ 4፡13 15-18

## 3. የእውነተኛ መሪ መስፈርቶች

3.1 በእግዚአብሔር የተጠራና ራዕይ ያለው ኤፌ 4፡11, የሐዋ 26፡17-19

3.2 ራዕዮን ሊሰራ ያለውን በግልፅ ያስረዳል ፡፡ ነሕ 2፡17-18

3.3 ራዕዮን በመታዘዝ ይወስናል ዘፍ 6፡13-18



3.4 እግዚአብሔር የሰጠውን ራዕይ ለሕዝቡ በግልፅ ያስረዳል ዘፀ 4፡ 30-31

3.5 ከባድና ሐይለኛ ለሰው የሚመስለውን ሁሉ በአምላኩ በመታመን ያሳልፈዋል 1ሣሙ 17 ፡ 45 -47, 2 ነገስት 3፡17-18

3.6 ፍቅር ያለው ነው ዘፅ 32, 32, ሮሜ 9፡1-2,

3.7 ትሁትና ሥልጣን ይገባኛል ብሉ የማይከራከር ነው ፊል 2-1-11

3.8 ተስፋ የማይቆርጥ ነው ዕብ 10፡23, 1ኛ ቆሮ 1፡9

3.9 ያንፃል እንጅ የሰራውን አያፈርስም ሮሜ 1፡11-12

3.10 እግዚአብሔር በሚሰራው የሚደሰት ነው መዝ 27፡4, 2ቆሮ 8፡21-24

3.11 ሌሎች የእግዚአብሔርን ሐሳብ እንዲያዩ ያደርጋል፡ ዳን 2፡27-30

3.12 እግዚአብሔርን በመፍራት በፅድቅ እንጅ በአድልኦ ምንም አያደርግም 1ኛ ሣሙ 30፡23-24,

3.13 ሰዎች ወደውና ፈቅደው በእምነት እንዲከተሉ ያደርጋል ዮሐን6፡67-69, 21፡15-17

3.14 እግዚአብሔር የሚጠላውን ይጠላል ይንቀውግል ዘፅ 32፡21-29, ዳን 5፡16-17

3.15 ራሱን የሚቆጣጠርና የሚገዛ ነው 2ጢሞ 1፡7

3.16 አይቸኩልም እግዚአብሔርን በመጠበቅ ያደርጋል፡፡ ዕንባቆ 2፡1-3 2ኛ ጢሞ 4፡7-8

3.17 ጥፋቱ ሲነገረው ለመታረም ፈቃደኛ ነው 2ኛ ሣሙ 12፡7-15

3.18 በተሰጠው ፀጋና መሪነት ወሳኝ ነው ሐዋ 20፡24

3.20 እስከ መጨረሻው ይፀናል፡፡ ማቴ 24፡ 12, 1ኛ ቆሮ 13፡6,



## ክፍል 2 የቃሉ መረዳት አስፈላጊነት

ምዕራፍ አምስት የቃሉ መለኮታዊ ሥልጣኑና ሀይሉ

1. ክርስቲያን አገልጋይ ቃሉን ለምን ያውቃል ?
2. የእግዚአብሔር ቃል ምን ዓይነት ተግባራትን በሕይወታችን ያደርጋል
3. የእግዚአብሔር ቃል በምን ተመሰሏል
4. የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅና ለመረዳት የሚረዱ መስፈርቶች

ምዕራፍ ስድስት የቃሉ እውነት የተረጋገጠው በመፈፀሙ ነው

1. ስለ ኢየሱስ በተነገረው የትንቢት ቃል

ምዕራፍ ሰባት የእግዚአብሔር የመለኮት አንድነት

1. የእግዚአብሔር አብ የበላይነት በወልድ ላይ
2. የእግዚአብሔር ወልድ ፍፁም ሰውነቱና አምላክነቱ
3. እግዚአብሔር ወልድ ለቤተክርስቲያን ምን ሰጠ
4. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምን ሰጠ

## ምዕራፍ አምስት

## የቃሉ መለኮታዊ ሥልጣኑና ሀይሉ

ባለንበት በዚህ ዓለም ላይ እግዚአብሔር የእኔ የሚላቸው ግዕከሎች /Institutues/ አለው እነርሱም ቤተሰብ፣ መንግሥትና፣ ቤተክርስቲያን ናቸው በነዚህ አማካኝነት እግዚአብሔር ፈቃዱንና ሀሳቡን ያከናውናል።

ቃሉን መረዳት ለአገልጋይ ዋነኛ ነገር ነው መንፈሳዊ አገልጋይ የራሱና የሌላው ነገር አገልጋይ ሳይሆን የቃሉ አገልጋይ ነው ከዚህ ውጪ የሆነ አገልግሎት ያስታል ከፈቃዱና ከመስመርም ያወጣል።

5.1 የእግዚአብሔር ቃል ስንል መለኮት የሆነ ሀሳብ ያለው በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሰው ልጅ ደህንነት እግዚአብሔር ሀሳቡን የገለፀበት መጽሐፍ ነው። 2ኛ ጴጥ 1:21, ዘፀ 17:14, ኤር 30:2, 2ኛ ሣሙ 23:2 2.ጢሞ 3:15-17

5.2 የእግዚአብሔር ቃል በእውነት የተሞላ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እውነተኛውን ነገር የሚያስተምር መለኮታዊ እውነት የተገለፀበት ነው። ሉቃ 24:26-27, 44-45,1ኛ ቆሮ 2:11-14, ዮሐን 16:12-15, የሐዋ 17: 1-3

5.3 የእግዚአብሔርን ጥበብ በመግለፅ የሰውን የልቦና ዐይን ያበራል የእግዚአብሔርን ማንነትና ክብሩን ይገልፅልናል። መዝ (119)18, ኤፌ 1:17-18

5.4 እስትንፋስ መለኮት የሆነ የመጨረሻ ሥልጣን ያለው ቃል ነው። 2ሣሙ 23:2 ዳን 10:21 ማቴ 24:35 2ኛ ጴጥ 1:10-21 2ጢሞ 3:15-17

## 1. <u>ክርስቲያን አገልጋይ ቃሉን ለምን ያውቃል ?</u>

1.1 የሚያመልከውንና የሚያገለግለውን አምላክ ለማወቅና ለመረዳት ጌታ ራሱን የገለጠው በቃሉም ስለሆነ ዮሐን 1:13, ዕብ 1:2 ራዕይ 19:13

1.2 የእግዚአብሔር ቃል የሕይወት ቃል ስለሆነ ዮሐን 6:63, ፊል 2:15-16

1.3 የእግዚአብሔር ቃል የእውነት ቃል ስለሆነ ዮሐን 1:14, ኤፌ 1:13, ያዕ 1:18

1.4 የእግዚአብሔር ቃል የእምነት ቃል ስለሆነ ሮሜ 10:8,17

1.5 የእግዚአብሔር ቃል ለዘለዓለም የሚኖር ስለሆነ መዝ (119)-89, ማቴ 24:35

1.6 የእግዜአብሔር ቃል ለዘለዓምም ዕድትን ስለሚያስረግጥ መዝ(119):(142)1ቆሮ 6-11

1.7 የእግዚአብሔር ቃል የሚቀድስ ስለሆነ ኤር 1:4-5, ዮሐን 15:3, ኤፌ 5:26



## 2. <u>የእግዚአብሔር ቃል ምን ዓይነት ተግባራትን በሕይወታችን የደርጋል</u>

2.1 የዘለአለም ሕይወትን መስጠትና ማኖር ዮሐን 8:51, 1ዮሐ 2:17

2.2 እግዚአብሔርን እንዳንበድል ቃሉን በልባችን ይሰውራል። መዝ (119):11

2.3 የእግዚአብሔር ቃል በድል እንድንወጣና እንድንገባ ያደርገናል። ዘፀ 27:21, መዝ 119-(105)

2.4 ማስተዋልን ይሰጣል። ዳን 10:11, መዝ (119):97-105

2.5 እግዚአብሔር በቃሉ ወደ እኛ ይመጣል። ዘፍ 15:1, ኤር 1:4-5

2.6 ትዕግስትን ይሰጠናል ራዕይ 3:10

2.7 የእግዚአብሔር ቃል በእግዚአብሔር መንፈስ በኩል ይናገራል። 2ኛሣሙ 23-2

2.8 ጠላትን ለመምታት ጋሻ ነው ኤፌ 6:16-17, ማቴ 4:4

2.9 የሚፈውስ ቃል ነው። ሉቃ 7:7

2.10 እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ የሚገልፅበት ነው። ዮሐን 14:21

## 3. <u>የእግዚአብሔር ቃል በምን ተመስሏል ?</u>

3.1 በምግብ ሉቃ 4:4, ዮሐን 6:35 ሕዝ 3:1-3

3.2 በእሣት ኤር 23:29, ሉቃ 24:32

3.3 በመስታወት ያዕ 1:23

3.4 በዘር ሉቃ 8:11, 1ኛጴ 1:23

3.5 በወተት 1ኛ ጴጥ 2:2

3.6 ከብርና ከወርቅ በሚበልጥ መዝ 19:7-10, ኢዮብ 28:1

3.7 ከማርና ከወለላ በሚጣፍጥ መዝ 19:10 ራዕይ 10:10

3.8 ከአልማዝና እንቁ በከበረ ማቴ 7:6 መዝ (119):(127)
3.9 በመልሕቅ ዕብ 6:17-19
3.10 በኮከብ 2ኛ ጴጥ 1:19
3.11 በሸክላ ሰሪ ኢሣ 29:16-17

4. <u>የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅና ለመረዳት የሚረዱ መሠረታዊ መስፈርቶች</u>

4.1 ቃሉን መስማት ማቴ 17:5, ሉቃ 11:28, ሕዝ 3:12
4.2 ቃሉን ማንበብ ኢሣ 34:16, ዮሐን 5:39, 2ኛ ጢሞ 3:15-17
4.3 ቃሉን ማመን ማር 1:15, ዮሐን 4:50, ኢሣ 26:4, ሮሜ 10:8
4.4 ቃሉን ማጥናት 2ጢሞ.2:15, የሐዋ 17:11, 1ኛ ጴጥ 1:10
4.5 ቃሉን ማሰብና ማሰላሰል ዘዳ 6:6, ኢያሱ 1:8, መዝ 1:1-3
4.6 ቃሉን መታዘዝ ዘዳ 13:6-11, የሐዋ 5:29, ሮሜ 6:17-18
4.7 ቃሉን ማስተማር ዘዳ 6:7, የሐ 20:20, 2ኛ ጢሞ 4:1



## <u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## <u>የቃሉ እውነት የተረጋገጠው በመፈፀሙ ነው</u>

6.1 ስለ ኢየሱስ በተነገረው የትንቢት ቃል

| *ትንቢት ቃል* | *የተፈፀመው* |
|---|---|
| 1. ከሴቲቱ የሚወለደው ዘፍ 3:15 | ገላ 4:4 |
| 2. የሴም ዘር ዘፍ 9:26 | ሉቃ 3:36 |
| 3. የአብርሐም ዘር ዘፍ 22.18 | ማቴ 1:1 |
| 4. የይስሀቅ ዘር ዘፍ 26:1-4 | ሉቃ 3:34 |
| 5. የያዕቆብ ዘር ዘፍ 8:13-14 | ሉቃ 3:34 |
| 6. የይሁዳ ነገድ ዘፍ 49:10-12 | ዕብ 7:14, ራዕይ 5:5 |
| 7. የእየሱስ ቤተሰብ ኢሣ 11:1-2 | ራዕይ 5:5, ማቴ 1:6 |
| 8. የዳዊት አምላክ የዳዊት ልጅ መዝ (110):1 | ራዕይ 22-16,ማቴ 22:41-46 |
| 9. ከድንግል የሚወለድ ኢሣ 7:14, ኤር 31:22 | ማቴ 1:18-23 |
| 10. አዲስ ነገር መፍጠር ኤር 31:22 | ሉቃ 1:34-35 |
| 11. ሀያል አምላክ ኢሣ 9:6-7 | ዮሐን 1:1-3, 14 |
| 12. ቤተልሄም እንደሚወለድ ሚክ 5:2 | ማቴ 2:1-8 |
| 13. ስለ መሲሁ መቀባት ኢሣ 61:1-4 | ሉቃ 4:16-22 |
| 14. እንደ ሙሴ ያለ ነብይ ዘዳ 18:18 | ዮሐን 6:14 |
| 15. ንጉስና ሕግ ሰጭነቱ ዘፍ 49:10 | ማቴ 5:5-7 |
| 16. የሰማነው ነገር ማን አምኗል ኢሣ 53-1 | ዮሐን 12:37-38 |
| 17. በእግዚአብሔር ስም ይናገራል ዘዳ 18.19 | ዮሐን 5:43 |
| 18. ወደ መቅደሱ ይመጣል ሚል 3:1 | ሉቃ 2:25-32 |
| 19. መሪዎች ይቃወሙታል መዝ (118):22 | የሐዋ 4:1-12 |
| 20. ከሰላሣ አመት ጀምሮ ዘኊ 4:3 | ሉቃ 3:23 |
| 21. ሦስት ዓመት ተኩል ዳን 9:24-27 | አራቱ ወንጌል |
| 22. የእግዚአብሔር ቃል በስልጣን ይናገራል ዘዳ18:18 | ዮሐን 8:28-38 |
| 23. በሰላሣ ብር እንደሚሸጥ ዘካ 11:13 | ማቴ 27:3-4 |
| 24. የሚያስታርቅ ይሆናል ዳን 9:24 | 2ኛ ቆሮ 5:18-21 |

25. ይመቱታል ኢሣ 50፡6 ማቴ 26፡67-68
26. እንደሚሸጥ ዘካ 11፡13 ማቴ 27፡6-10
27. ወደ ግብፅ ይወሰዳል ሆሴዕ 11፡1 ማቴ 2፡12-15
28. እንደተረገመ ሰው ይሰቀላል ዘዳ 21፡23 ገላ 3፡10-13, 1ኛ ጴጥ 2፡24
29. መበስበስን አያይም መዝ 16፡10 የሐዋ 2፡24-32



## ምዕራፍ ሰባት

## የእግዚአብሔር የመለኮት አንድነት

እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ፈጣሪ የማይወሰን ፍፁም የማይለወጥ እራሱን በሦስት አካል በአብ፣ በወልድና፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የገለፀ ነው ዘፍ 1፡26, 11፡7, ዘዳ 6፡ 4-5, መዝ 90 2, 147፡ 5, ኢሣ 40፡28, ሚል 3፡6, መዝ 139፡ 7-12, ዮሐን 17፡1 ኤፌ 4፡7

1. **እግዚአብሔር አብ ለወልድ የሰጠው የበላይነት**

1.1 እግዚአብሔር አብ በፍቅሩ ለሰው ልጆች በሰጠው ተስፋ መሰረት ለልጁ በሁሉ ላይ የበላይነትን ሰጠው፡፡ ዘፍ 3፡15, 17፡1, ኢሣ 7፡14,ማቴ 1፡21-25 ዮሐን 1፡12, 3፡16

1.2 ዓለም ሁሉ በልጅ እንዲድን እግዚአብሔር አብ ለወልድ ሰጠው ዮሐን 1፡29, የሐ 4፡12, ዮሐን 3፡16, 2ኛ ቆሮ 5፡17

1.3 እግዚአብሔር አብ በአካሉ ላይ የበላይነት እንዲኖረው ሰጠው 1ኛ ቆሮ 12፡6 ፊል 2፡8-11

2. **የእግዚአብሔር ወልድ ፍፁም ሰውነቱና አምላክነቱ**

እግዚአብሔር ወልድ ፍፁም ሰውና አምላክ የሆን በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም መወለዱን የሰው ልጆች ሁሉ

አዳኝና ቤዛ በመሆን በመስቀል ላይ ሞቶ በሦስተኛው ቀን መነሣቱን ከሞትም ከተነሣ በኋላ ሕያው ሆኖ እየታያቸው ከተመላለሰ በኋላ በክብር ወደ ሰማይ የወጣ ያረገ መሆኑን የሚያምኑትን ሁሉ ሊያማልድ በሕይወት መኖሩን ሊታመንበት የሚገባ እውነት ነው። ዘፍ 3፡15, ገላ 4፡4, ማቴ 1፡20-23, ማቴ 28፡6, የሐዋ 1፡3, 1ኛ ቆሮ 15/3-8, የሐዋ 1፡9-11, ኢሣ 53 5-6 , ሉቃስ 24፡5 ዮሐን 1፡1-4 የሐዋ 17፡31, 1ኛ ጤም 3፡16, ሉቃ 1፡35, ኢሣ 9፡6-7, ሮሜ 8፡34, 1ኛ ጤሞ 2፡5 ዕብ 7፡25, 1ኛ ዮሐን 2፡1-3, በዳግም ምፃቱም በሙታንና በሕያዋን ላይ ሊፈርድ የነገሥታት ንጉስ አብ የጌቶች ጌታ ሆኖ የሚገለፅ አምላክ ነው።

ዳን 7፡27, 1ኛ ጢሞ 6፡13, ራዕይ 19፡16, ማቴ 24፡30-31, 1ኛ ተሰ 4፡16-18, 2ኛ ቆሮ 5፡10, ሮሜ 14፡10, ራዕይ 20፡4

## 3. <u>እግዚአብሔር ወልድ ለቤተክርስቲያን ምን ሰጠ</u>

3.1 ሕይወቱን ሰጠ። ኤፌ 5፡23 -27
3.2 መንፈስ ቅዱስን ሰጠ ዮሐን 16፡13 የሐዋ 5፡32
3.3 አምስቱን የአገልግሎት ስጦታዎችን ሰጠ ኤፌ 4፡11
3.4 ሌሎች የተለያዩ ስጦታዎችን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ ኤፌ 4፡8-16, 1ኛ ቆሮ 12፡5



## 4. <u>እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምን ሰጠ</u>

መንፈስ ቅዱስ መንፈሣዊ አካል ያለው መለኮት በመሆን ሕይወትና ፀጋ የሚሰጥ አምላክ ነው። ዘፍ 1፡2,2፡7, ኢዮብ 33፡4,የሐዋ 3፡3-4,ማር 16፡17, የሐዋ 2፡4 1ኛ ቆሮ 12፡11, ኤፌ 2፡8, ዮሐን 14፡15-17

4.1 ስጦታን ሰጠ። 1ኛ ቆሮ 12፡4, 7-11
4.2 እንዲመስክሩ ሀይልን ሰጠ የሐዋ 1፡8, 1፡1-4,ዮሐ ፡ 15-26
4.3 ለሚላኩ መልዕክትን ሰጠ። የሐዋ 13፡4 ዮሐን 1፡31-33

የእግዚአብሔር አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ክፍል ሥራ የሆነ ሥዕላዊ መግለጫ

እግዚአብሔር አብ

ዮሐ 3፡16

እግዚአብሔር ወልድ

ኤፌ 4፡"11-16 , 5 ፡25

ሐዋሪያት ነብያት ወንጌላዊ መጋቢ አስተማሪ

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሐዋ 5፡32

1ኛ ቆሮ 12 ፡ 1-11

| | | |
|---|---|---|
| ትንቢት | እምነት | ጥበብ |
| ልሳን | ታአምራት | እውቀት |
| መተርጎም | መፈዎስ | መለየት |



## ምዕራፍ ስምንት

## እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

እግዚአብሔር በአምላክነት፣ በባህርይ፣ በሀይል፣ በዘላለማዊነት አንድ ሆኖ በሦስት አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ነው መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ከዘለዓለም የሚሠርጽ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ እንደ አምላክ ተገልጧል ስለ አምላክነቱም ሲመሰክርለት ሐዋ 5፡3-4 ለመንፈስ ቅዱስ መዋሸት ለአምላክ የመዋሸት ያህል ነው ተብሏል ሰውን ለዳግም ልደት የሚይበቃ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ከሚፈፅማቸው አምላክ መሆኑን ከሚያሳየን ተግባራቶች መካከል ዓለምን መፍጠሩና የተለያዩ ተግባራትን ማከናወኑ ነው፡፡

1. <u>መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ዓለም ውስጥ</u>

1.1 ፈጣሪ ነው ዘፍ 1፡2,2፡7, ኢዮብ 33፡4
1.2 እግዚአብሔር ነው፡፡ ዮሐን 4፡24
1.3 ሁሉን የሚያውቅ ነው ኢሣ 40፡13,1ቆሮ 2፡10-11
1.4 በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ነው፡፡ መዝ 139፡7-10
1.5 ዘለዓለማዊ አምላክ ነው፡፡ ዕብ 9-14

## 2. ሕያው የሆኑ የመንፈቅ ቅዱስ ሥራዎች

2.1 ፊልጶስን ዮሐንስንና ጴጥሮስን ሲናገር የሐዋ 8:29, ራዕ ይ 2:7
2.2 በርናባስንና ሳኦልን ሲጠራ /ሲለይ/ የሐዋ 13:2,4
2.3 በርናባስንና ጳውሎስን ሲልክ የሐዋ 13:4
2.4 ጳውሎስንና ስላስን ሲከለክል የሐዋ 16:6-7
2.5 አማኞችን ሲያስተምር ዮሐን 14:26, 1ኛ ዮሐ 2:27
2.6 ለአማኞችና ለቅዱሳን ሲገልጽ ሮሜ 8:26-27
2.7 ለእግዚአብሔር ልጆች ሲያረጋግጥ ሮሜ 8-14-17, ገላ 4:7
2.8 ለስምዖን ሲያስረዳ ሉቃ 2:26
2.9 የሚያምኑትን ሁሉ ሲሞላ የሐዋ 2:4, 4:31,
2.10 አማኞችን ሁሉ ሲያትም ኤፌ 1:13
2.11 በተቀበሉት ሁሉ መኖሪያና ማደሪያ ሲያደርግ 1ኛ ቆሮ 3:16-17, 2ኛ ቆሮ 5:5

## 3. የእግዚአብሔርነት ባሕሪው

3.1 ሕያውነቱ ሮሜ 8:2, የሕይወት መንፈስ ኢዮብ 33-4
3.2 የእውነት መንፈስ ዮሐን 3:3-5
3.3 የፍቅር መንፈስ 1ኛ ዮሐን 4:8, ሮሜ 5:5, 15:30
3.4 ዘለዓለማዊነት ዕብ 9:14 የዘለዓለም መንፈስ
3.5 ቅዱስ መንፈስ ኤፌ 4:30 ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ



## 4. ሕያውነቱን የሚገልጡ አስረጂዎች

መንፈስ ቅዱስ ስሜት ያለው ነው ስንል አንዳንድ ሰዎች ደምና ሥጋ እንዳለው ሰው አድርገው የሚገልፁትን የተሣሣተ አመለካከት አይደለም ሆኖም ግን ሕያውነቱን ለመግለፅ በአስረጂነት የተጠቀሰው አካል የሚለው ከሥራው ጋር የተያያዘ መሆኑን ለመግለፅ ነው፡፡

አካል ያለው የሚደረግበት የተለያዩ ነገሮች አሉ እንደዚሁም የመንፈስ ቅዱስን አካልነት በአስረጂነት የሚሰጡ ቃሎች

4.1 መሰደብ ማቴ 12:31, ማር 3:29
4.2 ማታለል የሐዋ 5:3
4.3 መፈተን የሐዋ 5:9
4.4 ማሳዘን ኤፌ 4:30
4.5 ማክፋፋትና ማጥላላት ዕብ 10:29
4.6 ማስመረር ኢሣ 63:10
4.7 ማጥፋት 1ኛ ተሰ 5:19
4.8 አለመሰማትና እልከኝነት ዕብ 3:1-9, ዘፅ 17:7
4.9 መካድ ገላ 3:5, ዕብ 6:4-6
4.10 መከራከር የሐዋ 6:9-10

## 5. መንፈስ ቅዱስ ለማን ይሰጣል ? 1ኛቆሮ 6:11

5.1 ከመንፈስና ከቃሉ ዳግም ለተወለዱት ዮሐን 3:3-5, 1ኛ ጴጥ 1:23
5.2 የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑት ሁሉ ሮሜ 8:14, ገላ 4-7

5.3 መንፈስ ቅዱስን ለሚለምኑት ሁሉ ሉቃ 11፡13, ዮሐን 3፡34

5.4 መንፈስ ቅዱስን እንደተስፋ ቃሉ ለሚጠብቁት ሉቃ 24፡49, የሐዋ 2፡1-4

5.5 መንፈስ ቅዱስን ለሚታዘዙት ሁሉ የሐዋ 5፡32

5.6 መንፈስ ቅዱስን ለሚጠሙት ሁሉ ኢሣ 55፡1,ዮሐን 7፡37-39

5.7 መንፈስ ቅዱስ ለሚለው የሚመሰከሩ ሁሉ የሐዋ 1-8, ዮሐን 15፡26

5.8 የመንፈስ ቅዱስን እውነት ለሚፈልጉት ሁሉ ዮሐን 16፡13

5.9 የመንፈስ ቅዱስን ትምሕርቱን ለሚፈልጉት ሁሉ ዮሐን 14፡26/፫ዮሐን 2፡27

5.10 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን ለሚፈልጉት ሁሉ 1ኛ ቆሮ 14፡1

5.11 መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ አካል ሁሉ የሚሰጥ ነው 1ኛቆሮ 12፡4-7

5.12 መላቱና ደስታውን ለሚቀበሉት ሁሉ ሉቃ 10፡21, የሐዋ 13፡52

6. <u>መንፈቅ ቅዱስ ለአገልግሎታችን ጥቅም (ፍሬ) ይሰጣል፡፡</u>

6.1 የጥበብ መንፈስ እግዚአብሔርን ለማወቅና ለመፍራት ኢሣ 11፡2, ኤፌ 1፡17

6.2 የእውቀት መንፈስ ተረድተን እንድናገለግለው ኢሣ 11፡2, 1ኛ ቆሮ 12፡8



6.3 የምክርና ሐይል መንፈስ ከእኛ እንዳልሆነ እንድናውቅ ኢሣ 11፡2, ዘክ 4-6

6.4 የፀጋ መንፈስ የስራችን ፍሬ እንዳይደለ እንድናውቅ ዘካ 12፡10

6.5 የፍርድ መንፈስ ተጠንቅቀን እንድንኖር ኢሣ 4፡4

6.6 የሚያጣራና የሚያቃጥል መንፈስ ኢሣ 4፡4, ማቴ 3፡11-12

6.7 የሐይል መንፈስ ሁሉን የሚችልና የሚያስችል ሉቃ 1፡35, 24፡49

6.8 የመፅናናት መንፈስ አዝነን እንዳንኖር ዮሐን 14፡16, 26, 15፡26, 16፡7

6.9 የእውነት መንፈስ እውነትን የሚገልፅ ዮሐን 14፡17, 16፡13

6.10 የፍቅርና ሐይል ራስን የመግዛት መንፈስ 2ጢሞ 1፡7, ገላ 5፡23

6.11 የእምነት መንፈስ በእምነት እንድናገለግል 2ኛቆሮ 4፡13

6.12 የተስፋና የቃል ኪዳን መንፈስ ኤፌ 1፡13-14, ሮሜ 15፡13

6.13 የክብር መንፈስ በእኛ ክብሩን የሚገልፅ 1ኛ ጴጥ 4፡14

6.14 የትንቢት መንፈስ በመንፈስ የሚያናግር ራዕይ 19፡10

6.15 የቅባት መንፈስ ሌሎችን ለማፅናናት 2ኛ ቆሮ 1፡2-22, 1ኛ ዮሐን 2፡27

6.16 የላከንን ጌታ በመንፈስ ቅዱስ ያመለክተናል ዮሐን 1፡31-33,

6.17 ጌታን በመንፈስ በመሆን የመልክቱን ድምፅ እንሰማለን፡፡ ራዕይ 1፡9-20

6.18 ኢየሱስን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሁነን ና እንድንሰው፡፡ ራዕይ 22-17

## 7. <u>መንፈስ ቅዱስ በእየሱስ ክርስቶስ ሕይወት</u>

7.1 እየሱስ ክርስቶስ ከድንግል እንዲወለድ በመንፈስ ቅዱስ ተነገረ ኢሣ 7፡14

7.2 እየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ተወለደ ሉቃ 1፡35, ማቴ 1 18-20

7.3 እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ ዮሐን 3፡34

7.4 እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ መቀባቱ ሉቃ 4፡18, ኢሣ 61፡1

7.5 እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተመራ ማቴ 4፡1, ሉቃ 4፡1

7.6 እየሱስ በመንፈስ ተናገረና አስተማረ ሉቃ 4፡18

7.7 እየሱስ በመንፈስ ሐይል ተዘዋወረ ሉቃ 4፡14

7.8 እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐይል በሽተኞችን ፈወሰ ሉቃ 4፡18

7.9 እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐይል አጋንትን አስወጣ ማቴ 12፡28

7.10 እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ፀደቀ 1ኛ ጢሞ3፡16

7.11 እየሱስ በዘለዓለም መንፈስ መስእዋት ሆኖ ቀረበ ዕብ 9፡14

7.12 እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ከሞት ተነሣ ሮሜ 8፡1, 1ኛ ጴጥ 3፡18

7.13 እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ደቀመዛሙርቱን አዘዛቸው የሐዋ 1፡2



7.14 እየሱስ ቤተክርስቲያንን በመንፈስ ቅዱስ አጠመቃት የሐዋ 1፡5,8,

7.15 እየሱስ ቤተክርስቲያን በመንፈስ ሲያመለክትና ሲያስተዳድር ራዕይ 2፡7,11

7.16 እየሱስ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስም መጣ ሉቃ 3፡21-22,ዮሐን1 32-33

## 8. <u>መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ</u>

8.1 ከመንፈስ ዳግም በመወለድ ይጀምራል ዮሐን 3፡3-6

8.2 የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ ይሆናል 1ኛቆር 3፡16-17, ሮሜ 8፡9

8.3 መንፈስ ቅዱስ የዘለዓለም ሕይወት ያረጋግጥለታል ሮሚ 8-16

8.4 በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ይሞላል የሐዋ 2፡4,1ኛቆር 12፡11,ኤፌ 5፡18

8.5 በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ በአዲስ ቋንቋም ያናግረዋል ይሰጠዋል፡፡ የሐዋ 2፡1-4, ማር 16፡17,1ኛቆር 14፡2, 4,18, 12፡13

8.6 መንፈስ ቅዱስ አማኙን ይናገረዋል፡፡ የሐዋ 8፡29, ራዕይ 2፡7,11

8.7 መንፈስ ቅዱስ አማኝን ያስተምራል ደግሞም ይመራዋል ዮሐን 16፡13

8.8 መንፈስ ቅዱስ ይጠራል ደግሞም ይልካል የሐዋ 13፡2-4

8.9 መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ መንፈስ ይመሰክራል ሮሜ 8-14

8.10 መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ እንዲመሰክር ሀይል ይሰጠዋል የሐዋ 1፡8

8.11 መንፈስ ቅዱስ ከሙታን ያስነሣል፡፡ ሮሜ 8፡11, 1ኛቆሮ 15፡47-51

8.12 መንፈስ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ያስመልካል ዮሐን 4፡23-24





ምዕራፍ ዘጠኝ የክርስቶስ አገልግሎት

1. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሐዋርያ
2. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ነበይ
3. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ወንጌላዊ
4. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መጋቢ /እረኛ/
5. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አስተማሪ

ምእዕራፍ አሥር የሀዋርያት አገልግሎት

1. የሀዋርያነት አገልግሎት
2. የነብይነት አገልግሎት
3. የወንጌላዊነት ስጦታ
4. የመጋቢነት /እረኛ/ አገልግሎት ስጦታ
5. የአስተማሪነት አገልግሎት ስጦታ

ምዕራፍ አሥራ አንድ የአገልግሎት ስጦታዎች ሥራ

1. ስም ትርጉምና ዓላማ
2. ሽማግሌ እና ሥራው
3. የዲያቆናት አገልግሎት

ምዕራፍ አሥራ ሁለት የተሳሳቱ አገልግሎቶች በአገልግሎት ስጦታዎች ስም

1. የሀሰተኛ ሀዋርያት አገልግሎት
2. የሀሰተኛ ነብያት አገልግሎት
3. የሐሰተኛ ወንጌላዊያን አገልግሎት
4. የሐሰተኛ መጋቢዎች /እረኞች/ አገልግሎት
5. የሐሰተኛ አስተማሪዎች አገልግሎት

ክፍል 3 አገልግሎት

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የክርስቶስ አገልግሎት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው እንዲያገለግሉት ሳይሆን ሊያገለግል ነው የመጣው እርሱ እውነተኛ አገልጋይ እና የእውነተኛ አገልግሎት ምሣሌ /Model/ ነው እየሱስ ለቤተክርስቲያን የሰጠውን አምስቱን የአገልግሎት ስጦታዎች /Ministerial gifts/ በእርሱ የምድር አገልግሎት ቀደም ብለው የታዩ ናቸው፡፡

1. እየሱስ ክርስቶስ እንደ ሐዋሪያ

ሀዋርያ የሚለው የአማርኛው ቃል ሲተረጉም የተላከ ማለት ነው፡፡ የዚህ ሥረው ቃል ማለትም የግሪኩ ቃል አፖስቶሊዩ ይለዋል ትርጉሙም የተላከ ማለት ነው፡፡

1.1 ኢየሱስ የተላከ ነው ዮሐንስ 3፡17, 34, 4፡34, 5፡36-38, 6፡29,57

1.2 ኢየሱስ እንዲያገለግል የተላከ ነው ማር 10፡45

1.3 ኢየሱስ የአብን ፈቃድ ሊያገለግል የተላከ ነው

1.4 ኢየሱስ ሐጢያተኞችን ሊያገለግል የተላከ ነው

## 2 ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ነብይ

ነብይ እግዚአብሔርን ወክሎ ለሰዎች መልዕክት የሚሰጥ ነው አንዳንድ ጊዜ ነብይ የእዚአብሔር ወኪል ወይም አፍ ይባላል ይህም በክርስቶስ ተገልጧል፡፡

2.1 ስለ ነብይነቱ እና ሙሴነቱ የተነገረ የትንቢት ቃል 1ኛ ሣሙ 2:10 ዮሐን 4:25-26, ዘዳ 18:18 ዘዳ 18:15-22, ዮሐን 5:36-37, የሐዋ 3:22-23 7:38
2.2 መለኮታዊ ቃል ተናገረ፡፡ ዮሐን 4:19,7:40, 17:8
2.3 በእግዚአብሔር ስም ተናገረ፡፡ ዮሐን 5:43, 8:55-58,12:13

## 3 ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ወንጌላዊ

ወንጌላዊ፡ የሚለው የስም ትርጉም ወንጌልን ከመስበክ ጋር የተገናኘና የተዛመደ ሲሆን ወንጌልን ላልሰሙ የሚመሰክርና ቤተክርስቲያንን የሚተክል በየቦታው ያለገደብ /ክልል/ እየተዘዋወረ ወንጌል ባልደረሳቸው የሚያደርስ ነው፡፡

3.1 ኢየሱስ የምስራች መልካም ዜና ተናገረ ኢሣ 40:9, 41:27:52:7
3.2 ኢየሱስ የፅድቅ ሰባኪ መዝ 40:9
3.3 የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት የፀጋ ቃል ሰበከ ኢሣ 61:1-2, ሉቃ 4:18-20 ቃል ሰበከ



## 4 ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መጋቢ /እረኛ/

እረኛ /መጋቢ/ በግሪክ ፖይመን በአዲስ ኪዳን 18 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን ቀጥታ የቃላት ትርጉም እረኛ ማለት ነው ጌታ እየሱስ የእረኞች አለቃ የሚጠብቅና የሚመራም እንደ ነበር ተገልጧል፡፡

4.1 ከእግዚአብሔር የተላከ እረኛ ኢሣ 40:1, ኤር 31:10, ሕዝ 34:23
4.2 የእረኞች አለቃ መክ 12:1, ሕዝ 34:23, 1ኛ ጴጥ 5:4
4.3 የነፍስ መልካም እረኛ ዮሐን 10:13, 1ኛ ጴጥ 2:25 ዮሐን 10:16
4.4 የሚጠብቅ የሚመግብ እረኛ መዝ 23:1, ሕዝ 37:24

## 5 ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አስተማሪ

አስተማሪ የሚለው ቃል በግሪክ "ዲዳስኮ" ሲባል ትርጉሙም መምራት /Instruct/ ማድረግ ማለት ነው በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ የተገለጠና በስፋት የታየም አገልግሎት ነበር፡፡

5.1 ትምህርቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ነው ዮሐን 3:2, 13:13
5.2 በእግዚአብሔር መንፈስና ፀጋ ያስተምር ነበር ሉቃ 4:18-19
5.3 ኢየሱስ በመስበክና በማስተማር ጊዜውን ያሣልፍ ነበር፡፡ ማቴ 4:25, 5:2, 9:35-36, 13:54, ሉቃ 13:10

5.4 በመለኮታዊ ሐይል እንደባለሥልጣን ያስተምር ነበር ዮሐን 7፡29, ማቴ 7፡28-29 ማር 1፡22



## ምዕራፍ አሥር
## የሀዋርያት አገልግሎት

ሀዋርያ የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ የአዲስ ኪዳን ቃል ሆኖ ተገልጿል ስለ ሀዋርያቶች ስናስብ በሁለት አይነት መልኩ በአዲስ ኪዳን ተገልጿል እነርሱም የበጉ ሀዋርያት እና የቤተክርስቲያን ሀዋርያት ናቸው የበጉ ክርስቶስ በምድር በአካል ተገኝቶ የመረጣቸው ብቻ ሲሆኑ የቤተክርስቲያን ሀዋርያት ተብለው የሚጠሩ ግን ከእነርሱ ውጪ ያሉትን ነው በእነዚህ ሁለት ዓይነት ሐዋርያት በክርስቶስ ሕይወት የታየው የሐዋርያ፣ ነብይ፣ ወንጌላዊ፣ መጋቢ፣ እና አስተማሪ አገልግሎት በእነርሱም ተደግሞ እንደነበር እንመለከታለን፡፡

### 1ኛ የሐዋሪያነት አገልግሎት እና ሥልጣን

1.1 እግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡና የተሾሙ ሐዋሪያትን ብቻ ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ ኤፌ 4፡11 1ኛቆሮ 12፡28,29
1.2 ትምሕርት ይሰጡ ነበር የሐዋ 2፡42
1.3 አስራሁለቱ የበጉ ሐዋሪያት ሉቃ 6፡12-13, ራዕይ 21፡14
1.4 ሐዋሪያት ከጌታ የሚጠሩና የሚላኩ ናቸው የሐዋ 9፡1-20
1.5 በርናባስ፣ ሲላስ፣ ቲቶ ጢሞቴዎስ የቤተክርስቲያን መልዕክተኞች /ሐዋርያ/ ነበሩ የሐዋ 13፡15 የሐዋ 15፡40 የሐዋ 16፡9 የሐዋ 15፡27 2ኛ ቆሮ 8፡16-24
1.6 አማባቸውና ድካማቸው ለአቢያተ ክርስቲያናት በየስፍራው ላሉት ሁሉ ነው፡፡ 2ኛ ቆሮ 11፡28, 1ኛ ጴጥ 1፡1-2, ራዕይ 1፡10-11

1.7 ሐዋሪያት ለክርስቶስ አካል ራዕይና መልዕክት አላቸው፡፡ ኤፌ 3፡1-9,4፡1-16

1.8 ቤተክርስቲያን ያቋቁማሉ ያደራጃሉ 1ኛ ቆሮ 9፡1-2, 11፡34

1.9 መንፈሣዊ ሹመት ይሰጣሉ 1ኛ ጢሞ 1፡18, 4፡14, 5፡22 2ኛ ጢሞ 1፡6, 4፡6

1.10 የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማርና በመስበክ ይደክማሉ 1ጢሞ 2፡7,2፡11

1.11 በቃሉ ክርስቲያኖችን ያሳድጋሉ፡፡ ኤፌ 4፡11-16, ቆላ 1፡25-29 ዕብ 6፡1-2, 1ኛ ጴጥ 2፡2

1.12 የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፀጋ ከእነርሱ ጋር ይሰራል፡፡ የሐዋ 8፡14 1ኛ ጢሞ 4፡14, የሐዋ 14፡23

1.13 የሐዋሪያት አገልግሎት ከሽማግሌዎችና ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በአንድነት ይሰሩ ነበር፡፡ 1ኛ ጴጥ 5፡1-5, 1ኛ ዮሐን 1፡1 3ኛ ዮሐን 1, ራዕይ 4፡4, 5፡8, 1ኛጢሞ 3፡ቲቶ 1

1.14 ለክርስቲያኖች የክርስቶስ ምሳሌዎች ነበሩ 2ኛ ቆሮ 11፡1ዕብ 3፡1

2. <u>2ኛ የነብይነት አገልግሎት ስጦታ</u>

2.1 እግዚአብሔር የነብያትን አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ፡፡ 1ኛ ቆሮ 12-28 1ኛ ቆሮ 12፡29

2.2 ነብይ ትንቢታዊ በሆነ መንገድም የእግዚአብሔርን ቃል የሚገልፅ የመንፈስ ቅዱስ መጠቀሚያ ነው የሐዋ 2፡14-21, 28፡32

2.3 የትንቢት መንፈስ የኢየሱስ ምስክር ነው ራዕይ 19፡10



2.4 በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራሉ፡፡ 2ኛ ጴጥ1፡ 20-21, 2ኛ ሣሙ 23-2 ዕብ 1፡1-2, 1ኛ ጴጥ 1፡10-11

2.5 ነብይ መለኮታዊ መገለፅ ይሰጣቸዋል፡፡ ኤፌ 3፡1-5

2.6 የነብይ የቃሉ መልዕክት አይወድቅም 1ኛ ሣሙ 3፡19-21

2.7 በራዕይ ያዩትን ሊመጣ ያለውን ይገልፃሉ፡፡ የሐዋ 21፡10-11 የሐዋ 11፡27-30

2.8 ለእግዚአብሔር መንፈስ ይታዘዛል 1ቆሮ 14፡32-33

2.9 የእግዚአብሔር ራእይ ይገልፃሉ 1ቆሮ 12፡6-9

3. <u>3ኛ የወንጌላዊነት ስጦታ</u>

3.1 ፊልጶስ የወንጌላዊነት ስጦታ ነበረው የሐዋ 21፡8-10, ኤፌ 4፡11

3.2 ጢሞቴዎስ የወንጌልን ሥራ ሥራህ አድርግ ተባለ 2ኛ ጢሞ 4፡5

3.3 የወንጌል መልክተኛ ማቴ 24፡14, ማር 16፡15-16, ኤፌ 2፡17, ራዕይ 14፡6

3.4 ወንጌላዊ ለክርስቶስ አካል መታነፅ የተሰጠ ነው ኤፌ 4፡9-11

3.5 ወንጌላዊ ለነፍሣት ሸክም አለው ፡፡ የሐዋ. 8፡1-

3.6 ወንጌላዊ ነፍሣትን የማምጣት ፀጋና ሀይል አለው ሉቃ 14፡33

3.7 የወንጌላዊ መልዕክት ግልፅና መልካም ዜና ማብሰር ነው፡፡ የሐዋ 8፡1

3.8 ቃሉን ይሰብካል የሐዋ 8፡4, 2ኛጢሞ 4፡1-2

3.9 ክርስቶስን ያስተዋውቃል፡፡ የሐዋ 8፡5, ሮሚ 1፡9

3.10 በወንጌል ሕብረት እንዲፀና ይፀልያል ሮሜ 1:9-12
3.11 የመንግስትን ወንጌል ይሰብካል:: ማቴ 24:14
3.12 በግለሰብ ደረጃም ወንጌልን ያስተዋውቃል የሐዋ 8:27-39
3.13 የጌታን ድምፅ ያዳምጣል:: የሐዋ 8:26
3.14 ወንጌል ለሁሉም እንደሚያስፈልግ ያውቃል የሐ 8:27
3.15 በመንፈስ ቅዱስ ይመራል:: የሐዋ 8:29
3.16 ወንጌልን ሰብኮ ወደ ውሳኔ ያደርሳል:: ዮሓን 4:28-29, ዮኅን 9:36-38, የሐዋ 8:35
3.17 በወንጌል ቃል የተዘጋጀ ነው:: ሮሜ 1:15, የሐዋ 8:30-34

## 4. 4ኛ የመጋቢነት /እረኛ/ አገልግሎት ስጦታ

4.1 ከእግዚአብሔር የሚሰጡ ናቸው:: ኤፌ 4:11
4.2 እረኛ ጠባቂና መሪ ነው የሐዋ20፡28
4.3 የበጎች ጠባቂ መጋቢ ይባላል ዮሐ 21:16-17
4.4 በጎቹን የሚያውቅ ነው ዮሐን 10:3
4.5 እረኛው የጊዜውን ቃል ይመግባል ያስተምራልም ዮኅን 10:3, 2ጢሞ 4:12
4.6 እረኛ በጎቹን ለሌባ ትቶ አይሸሽም ዮኅን 10:12
4.7 እረኛ ነፍሱን ለበጎቹ ይሰጣል:: ዮኅን 10:11
4.8 እረኛው የእረኞች አለቃ እንዳለው ያውቃል 1ኛጴጥ 5:1-5,
4.9 እረኛው ያስተዳድራል:: ማቴ 2:6, 1ጢሞ 5፡17-21
4.10 እረኛው በጎቹ የእግዚአብሔር እንደሆኑ ያውቃል:: 1ኛ ጴ5:2



4.11 እረኛው የበጎችን ድምፅ ያውቃል ዮሓንስ 10:26-27
4.12 እውነተኛ እረኛ ለጌታና ለሕዝቡም ይታመናሉ:: 1ኛ ቆር 4:1-2
4.13 ለበጎቹ ነፍስ ይጠነቀቃል ይራራል ዕብ 13:17, ማቴ 9:36
4.14 እረኛ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ራዕይ አለው:: ኤፌ 3:1-2

## 5. 5ኛ የአስተማሪነት አገልግሎት ስጦታ

5.1 እግዚአብሔር አስተማሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ 1ኛ ቆር 12:28, ኤፌ 4:11
5.2 የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራል ሮሜ 12:7, ማቴ 28:18-20, 1ቆር 4:17
5.3 አስተማሪ ቃሉን በማስተማር ያምናል በሥልጣንም ያስተምራል የሐዋ 2:4, 1ኛጢሞ 6:3, ማቴ 7:28-29, ማር 1:22
5.4 አስተማሪ የሚማር ነው:: 1ኛ ጢሞ 4:13, , ማቴ 4:4 ራዕይ 10:8-10,
5.5 አስተማሪ ለቃሉ የፀሎት ጊዜ የሚሰጥ የሐዋ 13:1-2 ኛ ቆር 2:13
5.6 አስተማሪ አስተማሪዎች ያሳድጋል 2ኛ ጢሞ 2:2
5.7 አስተማሪ ያስተማረውን ይኖራል:: 2ኛ ጢሞ 3:10, ሉቃ 24:19
5.8 አስተማሪ ለተማሪዎች ምሳሌ ይሆናል ዮሓን 13-12-5, 2ኛ ጤሞ 3:10
5.9 አስተማሪ እንደ ቃሉ ያስተምራል 1ኛ ጴ 4:11 ኤር 23:28

5.10 የሐሰት ትምህርትን በትምህርት ይቃወማል ማቴ 24፡11, 2ኛ ቆሮ 11፡13

5.11 አስተማሪ ለራሱና ለሌሎችም ይጠነቀቃል፡፡ 1ኛጢሞ 4፡15-16

5.12 የእግዚአብሔርን ቃል ከሐሰት ጋር አያቀላቅልም 2ኛ ቆሮ 4፡1-2



## ምዕራፍ 11

## የአገልግሎት ስጦታዎች ስምና ዓላማ

1. እነዚህን የአገልግሎት ስጦታዎች አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች ተብለው ተገልፀዋል በትክክል የምናየው በኤፌ 4፡11, ላይ ነው፡፡

ትርጉም

1.ሀ ሐዋሪያነት- አገልግሎት በመላክ "ገንቢ" ነው

1.ለ ነብይነት- "መምራት" የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማሳየት

1.ሐ ወንጌላዊነት - "መሰብሰብ" ወደ እግዚአብሔር መንግሥት

1.መ መጋቢነት- በእግዚአብሔር ቤት "መጠበቅ"

1.ሠ አስተማሪነት - በቃሉ መሠረት የሚያስይዝ ሆኖ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ እንደሆነ ቃሉ ይነግረናል፡፡

2. እነዚህ አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች አላማቸው ምንድነው ? ኤፌ 4፡12-16

2.ሀ ሁሉም የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅና በማመን ወደ ሚገኘው አንድነት ሙሉ ሰው ወደ መሆን እንዲያድጉ

2.ለ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመስራትና ለክርስቶስ አካል እንደ ሕንፃ ፍፁማን እንዲሆኑ

2.ሐ በስሕተት ሽንገላ ባለ ትምህርት ነፍስ በሕፃንነት ባለማወቅ እንዳይወሰዱ ለመርዳት

2.መ ሁሉም ወደ ክርስቶስ መሓትና እርሱን ወደ መምሰል እንዲደርሱ ለመርዳት

2. <u>የሽማግሌዎች አገልግሎት</u>

ሽማግሌ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "ዛኪን" በግሪክ "ፕሪስቡተሮስ" በግዕዝ ደግሞ ቀሳውስት ቀሲስ ተብሎ ተተርጉሟል

ሽማገሌ የሚለው የአማርኛችን ቃል አሻሚ ነው ምክንያቱም ወደ ቃሉ ስንሄድ ሽማግሌ-የዕድሜ-ቲቶ 2:2

የውክልና ዘፀአት 18:-2-27

ለሙሉ ጊዜ አገልጋይ /Over seer/ ጴጥ 5:1, 3ዮሐ.1

በተለይ የሽምግልና ሥራ የቡድን አገልሎትን የሚያመለክት ነው ይሄ የቡድን ሽምግልና (Team pastoral leadership) ነው::

ሽማግሌ ከቅድመ ክርስትና በፊት የነበረ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን በድህረ ክርስትና ይሰራበትም ነበረ አንድ የአገልግሎት ክፍል ነው::

2.1 የሽማግሌዎች አገልግሎት በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የነበረው ነው:: ዘኍ 11:16, የሐዋ 15:4-22,



2.2 የሽማግሌዎች ምርጫ በእግዚአብሔር አማካኝነት በነሙሴና ጳውሎስ ሕዝቡን ለማስተዳደር የሚሾሙ ናቸው:: ዘኍ 11:16 የሐዋ 15:4, 16 : 4-5, ቲቶ 1:5

2.3 ሽማግሌዎች የአስተዳደርና የገንዘብ ሥራን ሁሉ ይይዛሉ:: የሐዋ 11:30

2.4 ሽማግሌዎች ከነሙሴ ከሐዋሪያት ከዲያቆናት ጋር ያገለግላሉ:: ዘኍ 11:16 የሐዋ 15-22 ፊል 1:1

2.5 ሽማግሌዎች በቤተሰብ ኑሮአቸው ሁሉ ምሣሌ መሆን አለባቸው:: 1ኛ ጢሞ 3:1-7 ቲቶ 1:5-9, 1ኛ ጴጥ 5:3

2.6 ሽማግሌ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ለማስተማር የሚችሉ መሆን አለባቸው:: 1ኛ ጢሞ 5:17, ዕብ 13:7

2.7 የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከስሕተት የመጠበቅ ሐላፊነት አለባቸው:: የሐዋ 20:28 29, 1ኛ ጴጥ 5:2 ራዕይ 2:2

2.8 ሽማግሌዎች ለሕመምተኞች ለችግረኞች መፀለይ አለባቸው ያዕቆ 5:14-15

2.9 በሽማግሌ ላይ የሁለትና የሶስት ምስክርነት ካልተገኘ ክስና ወቀሣ አትቀበል ይላል 1ኛ ጢሞ 5:19

2.10 ሽማግሌ ስለ ድካማቸው አክብሩአቸው ይላል፡፡ 1 ጢሞ 5፡17, 1ኛ ተሰ 5፡12-13

2.11 ሽማግሌዎች ከጌታ ጋር ከአገልጋዮች ጋር ከሕዝቡ ጋር የእግዚአብሔር ከቡራን ናቸው፡፡ ራዕይ 4፡4-5, የሐዋ 15፡4, 1ኛ ጢሞ ? 5፡17

3. <u>የዲያቆናት አገልግሎት</u>

3.1 የዲያቆናት አገልግሎት ከአገልግሎት ክፍል አንደኛው ነው 1ኛ ጢሞ 3፡10-13 ፊል 1፡1

3.2 የዲያቆናት አገልግሎት ምርጫ በጌታና በአገልጋዮቹ አሳሳቢነት በሕዝቡ ተመርጠው በአገልጋዮቹ ይሾማሉ፡፡ የሐዋ 6፡1-6, 1ኛ ጢሞ 3፡10-13

3.3 ዲያቆናት ሕዝቡን እንደ ጌታ ዝቅ ብለው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ሉቃ 22፡26-27, የሐዋ 6፡1-6, ሮሜ 16፡1

3.4 ዲያቆናት በሕዝቡ ውስጥ ያለውን እንጉርጉሮ ለማስቀረት የሚሾሙ ናቸው የሐዋ 6፡1-7 1ኛ ጢሞ 3፡10-13

3.5 ዲያቆናት ሕዝቡን በቃሉ የሚያፅናኑና በእምነት አንድነት ለመስራት ምሳሌዎች ናቸው የሐዋ 6፡7-8, ሮሜ 16፡1-3



3.6 ዲያቆናት እስከ ሕይወት መስዕዋትነትን በመክፈል የእውነት ቃልና የፍቅር የትዕግስት ምሣሌ መሆን ይገባቸዋል የሐዋ 7፡54-60

3.7 ዲያቆናት ከሐዋሪያትና ከሽማግሌዎች ጋር በመሆን በመላላክና በመርዳት ያገለግላሉ፡፡ የሐዋ 6፡1-8, ሮሜ 16፡1-3, ፊል 1፡1

የዲያቆናት አገልግሎት እንደ ቃሉ ተቀብላ ቤተ ክርስቲያን ብትጠቀም መታነፅና አንድነት የነፍግት ወደ ጌታ መመለስ ከማጉረምረምና ከእንጉርጉር በመውጣት የክርስቲያኖች መመስረትና መታነፅ ይሆናል፡፡

<u>ማረጋገጫዎቹን በሐዋሪያት ሥራ እናገኛለን፡፡</u>

- ማጉረምረም ሲጠፋ ሕዝቡ ሲበዛ የሐዋ 6፡7
- የእግዚአብሔር ፀጋና ታእምር ሲገለፅባቸው የሐዋ 6፡8
- የተሰጣቸው ጥበብና መንፈስ የሚቋቋመው የለም የሐዋ 6፡9-10
- በተቋዋሚዎች ፊት የእግዚአብሔርን ክብር መግለጫዎች ይሆናሉ የሐዋ 6፡15
- የእግዚአብሔር ቃልና ስለ ጌታ ምስክሮች ነበሩ፡፡ የሐዋ 6፡7
- የእግዚአብሔርን ቃል በጥበብና እውቀት ለጉባኤ ሲያስረዱ ይኖራሉ የሐ 7፡1-53
- የእየሱስ ሕይወት ምሣሌዎች ሲሆኑ ታይተዋል የሐዋ 7፡56-60

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

### የተሳሳቱ አገልግሎቶች በአገልግሎት ስጦታዎች ስም

ስለ አገልግሎት ስናስብ አይነቱን በሁለት ልንከፍለው እንችላለን ይኼውም እውነተኛ እና ሐሰተኛ የሆነ አገልግሎት፡፡

እውነተኛው ለእግዚአብሔር ክብር እና ለሰዎች በረከትና ማደጊያ ምክንያቶች ናቸው ሐሰተኛ የሆነው አገልግሎት ግን ለግዚአብሔር ክብር የሆነ ሳይሆን ሌላውን የሚያከበር ለሰዎች በረከት ያልሆነ እዚአብሔር የሌለበት አገልግሎት ነው፡፡ በተለይ በመጨረሻው ዘመን የአገልግሎት ስጦታዎች /Ministerial gifts/ ከለላ በማድረግ የሚከናወኑ እውነተኛ የመሰሉ ግን ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች ይገለጣሉ እነዚህ መሳይ አገልግሎቶች ከእውነተኛው የሚለዩበትን በአርእስት እናያቸዋለን፡፡
እግዚአብሔር እነዚህን አገልግሎቶች ሲሰጥ ያመልከኝና ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቡን ልቀቅ እንዳለው እኛም ይህን ፀጋ ሲሰጠን ቀብረን ልናስቀምጣቸው ማይሆን ለጌታ ክብር ለቤተ ክርስቲያን በረከት ለእኛም በረከትና መፅናናት እንዲሆን በማለት እንደሆነ መታወቅ አለበት፡፡

1. <u>የሐሰተኞች ሐዋሪያት አገልግሎት</u>

1.1 አስመሳይ ሐዋሪያት ሐሰተኞች የተንኮል አገልጋዮች እራሳቸውን እንጅ መንጋውን የማይወዱ ከሐዲዎች የአፍ ሰዎች ናቸው፡፡ 2ኛ ቆሮ 11፡13

1.2 ሐዋሪያ ሳይሆን በሐሰት ሐዋሪያ ነን እያሉ ሕዝቡን ወደ ስሕተት ይመራሉ ራዕይ 2፡2

1.3 እነዚህ ሐሰተኞች የሚለያዩ ሥጋዊያን የሆኑ የአካሉን ሕብረት ይጎዳሉ ይሁዳ 1፡19

1.4 እነርሱ ዋና መሆን የሚፈልጉ ሌሎችን የማይቀበሉና ሌላው እንዳይቀበላቸው በሐሰት ሥም አጥፊዎች ናቸው፡፡ 3ኛ ዮሐ 9-10

1.5 ድሆችን ይንቃሉ ያዋርዳሉ ባለፀጎችን ለጥቅም የክብር ቦታ ይሰጣሉ ያዕቆ 2፡6

## 2 የሐሰተኞች ነብያት አገልግሎት

2.1 የበግ ለምድ ለብሰው የሚመጡ ነጣቂና በጎችና የሚጎዱ ተኩላዎች ናቸው ማቴ 7፡15

2.2 ብዙዎችን በማሣት ሕዝቡን የሚጎዱ ከእውነት የሚያወጡ ናቸው ማቴ 24፡11,24

2.3 ሐሰተኛ የክርስቶስ መልክተኞች ናቸው የተመረጡትን እንኳ ሣይቀር ሊያስቱ የሚችሉ ናቸው ማር 13፡22-23

2.4 የዋጃቸውን ጌታ በመካድ ሕዝቡን በመዳራትና በገንዘብ ጥቅም በማታለል ወደ ጥፋትና ሞት የሚወስዱ ናቸው፡፡ 2ጴጥ 2፡1-3 ዘኃ 22፡7



2.5 በሚናገሩት መንፈሣዊ መሰል አነጋገር ሕዝቡን በማሣት የተካኑ ሰርጎ ገብ ናቸው 1ዮሐን 4፡1

2.6 የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ሴሰኝነትና ጣኦት መዳራት የሚመልሱ ይህንም እያዩ ችላ በማለት የሚሰማሙ አይነት መሪዎች ናቸው፡፡ ራዕይ 2/20-23

## 3ኛ የሐሰተኞች ወንጌላውያን አገልግሎት

3.1 የአማኞችን ሕይወት የሚያናውጡ የክርስቶስንም ወንጌል የሚያጣምሙ መሣይ መልዕክተኞች ናቸው፡፡ ገላ 1-7

3.2 እነዚህ መለያየትንና መከፋፈልን የሚያመጡ ለሕዝቡ የማይራሩ ለገዛ ሆዳቸው ሲሉ እውነተኛውን የወንጌል ቃል የሚቃወሙ ሐሰተኛ ሰባኪዎች ናቸው፡፡ ሮሜ16፡17-18

3.3 እነዚህ ሐሰተኞች ወንጌላዊያን ወገንኝነትንና ዘረኝነትን በማንሣት በእውነተኛ የወንጌል መልክተኞች ላይ መከራና ችግር የሚያመጡ ናቸው፡፡ ፊል 1፡15-17

3.4 እንድ ሰው ወግና ፍልስፍና በሚመስል ሕዝቡን ከመንፈሣዊ ነገር ወደ ማይጠቅም ነገር የሚመልሱ አለማዊ ሐሣብ የያዙ ናቸው፡፡ ቆላ 2፡4,8 6, 18, 2ተሰ 3፡1-2

3.5 ለነፍሳት ግድ የሌላቸው ሞያተኞች ገንዘብን የሚወዱ ይህንንም በመመኘት ብዙ ሥቃይ የሚያመጡ ናቸው 1ጢሞ 6፡10 2ጴጥ 2፡3

## 4ኛ <u>የሐሰተኞች እረኞች አገልግሎት</u>

4.1 እግዚአብሔር ሣይጠራቸው በፍቃዳቸው የሚመሩ የመንጋውን ሕይወት የሚሰርቁ ወንበዴዎች ናቸው፡፡ ዮሐን 10፡1 ሕዝ 34-1-2

4.2 እነዚህ ሐሰተኞች እረኞች መንጋውን ጥለው የሚሸሹ ለነጣቂ ተኩላ አሣልፈው የሚሰጡ ናቸው፡፡ ዮሐን 10፡12-13

4.3 እነዚህ ሐሰተኞች እረኞች የጠፉትን በጎች የማይፈልጉ ጥቅማቸውንና ድሎታቸውን ብቻ የሚፈልጉ ናቸው ሕዝ 34፡3, 2ጤሞ 3፡4-5

4.4 እነዚህ ራዕይ የሌላቸው ሰማይ የተዘጋባቸው አገልጋዮችን የማያሣድጉ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳያውቁት የሚያደርጉ በእግዚአብሔር ቤት የሚደረገው ሐጥያት የማይፀየፉ መሪዎች ናቸው፡፡ / 1ጢሞ 2.22. 3:1-7

4.5 ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች መንጋውን ወደ ኋላ የሚመልሱ አጥፊዎች ናቸው፡፡ የሐዋ 20፡29-30

4.6 የአመፅን ደመወዝ እንዲሁም ተድላና ደስታ መዳራትንና ርኩሰትን ያስመኛሉ 2ኛጴ2 12-14



## 5ኛ <u>የሐሰተኞች አስተማሪዎች አገልግሎት</u>

5.1 እነዚህ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ከሐሰተኞች ነብያት ጋር በመስማማት አማኞችን የዋጃቸውን ጌታ በማስካድ ወደ መዳራት ጥፋት ይወስዳሉ፡፡ 2ኛ ጴጥ 2፡1-3

5.2 እነዚህ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ዋና መሆን የሚፈልጉ ጌታን ታምነው የወጡትን እውነተኛ አገልጋዮች ቤተ ክርስቲያን እንዳትቀበላቸው ክፉ ወሬ የሚያስወሩ ናቸው፡፡ 3ዮሐን 7-10, ፊል 1፡15-17

5.3 እነዚህ ሐሰተኞች አስተማሪዎች በሥጋ ምኞት የሚከተሏቸው ሥጋዊያን ክርስቲያኖች አዋሪዎችና አጫፋሪዎች አሏቸው 2ጴጥ 2፡1-3, 12-14 1ቆሮ3፡1-4

5.4 እነዚህ ሐሰተኞች የእግዚአብሔርን ቤት የንግድና የሸቀጥ ቤት በማድረግ በነፃ ተቀብላችሁ በነፃ ስጡ የሚለውን የወንጌልን ቃል ትተው ቅዱሱን የእግዚአብሔር ቤት ከአለም ጋር ያስማማሉ ጌታንም ለማስቆጣት ይነሣሉ፡፡ ዮሐን 2፡13-15, ማቴ 10፡8 ሮሜ 16፡17-18

5.5 የእግዚአብሔርን ቃል በመተው እነርሱ የሚያወጡትን ወግና ስርዓት በማስተማር ቃሉን ይሽራሉ፡፡ ከእዚሕም የሚብስ ብዙ ክፉ ነገር ያስፋፋሉ፡፡ ማር 7፡6-7, 13,

5.6 እነዚህ ሐሰተኞች ከሚናገሩት ቃል ይልቅ በፍሬአቸውና በአኗኗራቸው ይታወቃል፡፡ ማቴ 7፡15-20, 2ጢ 4፡3-4

## <u>ክፍል 4 ምክሮች</u>

ምዕራፍ አሥራ ሦስት ለአገልጋይና ለአገልግሎቱ ጠቃሚ ምክሮች

1. የፀሎት ጊዜ ለአገልጋዩ የሚሰጠው ጥቅም
2. ከእግዚአብሔር ራዕይ መቀበል ማግኘት አስፈላጊነቱ
3. ራዕይ እንዴት እንቀበላለን ?
4. ኪእግዚአብሔር የሆነ ራዕይ የሚከተሉትን ይመስላል
5. ከእግዚአብሔር የተሰጠን ራዕይ ሊጠፋ የሚችለው እንዴት ነው
6. ከእግዚአብሔር ያልሆነው ራዕይ እንዴት እንለየዋለን ?
7. እግዚአብሔር ቤቱን እንዴት በአገልጋይ እንደሚሠራ እንወቅ

ክፍል 4 ምክሮች

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## ለአገልጋይና ለአገልግሎቱ ጠቃሚ ምክሮች

1. የፀሎት ጊዜ ለአገልጋዩ የሚሰጠው ጥቅም

1.1 ከእግዚአብሔር አብ ጋር የምንገናኝበት ጊዜ ያስፈልጋል ለመንፈሳዊ ሥራ ድፍረት ለማግኘት ማቴ 14:23, ማር 6:46, ዳን 6:10-12

1.2 ኢየሱስ በማለዳ ለብቻው ከአብ አባቱ ጋር ጊዜ ያሳልፍ ነበር ፈቃዱን ለማገልገል ማር 1:35 ሉቃ 5:16

1.3 በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የመፀለይ ሚስጥር ከፈተና ይጠብቀናል ያድናልም:: ማቴ 4:1ሉቃ 4:1 ሮሜ 8:26-27,ኤፌ 6:18

1.4 የእግዚአብሔርን መልዕክት ለመቀበልና በእኛ እንዲናገረን እንዲሰራ መፀለይ ዮሐን 14:10, ዘፅ 24:12, 2ኛ ሣሙ 23:2

1.5 የእግዚአብሔርን ክብር እንድናይ በእኛ ስር የምናሳድጋቸው የታመኑ ሰዎችን ተተኪዎችን እንዲሰጠን የእግዚአብሔርንም ክብር እንዲያዩና እንዲያውቁት 9:28, ዘፅ 24:12-14, 2ኛ ጢሞ 2:1-2,2ኛ ነገስት 2:1-15

1.6 እግዚአብሔር እንደ ልቡ ፍቃድ የሚያገለግሉትን እንዲያስነሣና እንዲልክ 1ኛ ሣሙ 2:35, ኤር 3:15, 1ኛ ሣሙ 13:14

1.7 እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሚለያቸውን እንዲለይና እንዲጠራ የሐዋ 13:2-4 ኢሣ 6:8

1.8 እግዚአብሔር አምላክ በሉ ተናገሩ የሚለንን እንድንናገርና የተሰወረው ሚስጥር አምላካችን እንዲገልፅልንና እንዲናገረን

2ኛ ዜና 18:13, 1ኛ ነገስት 18:24, ዳን 2:17-27, 5:16-17,

1.9 የምንታመነውና የምንደገፈው አምላካችን ብቻ እንዲሆን ለመፅናት እንዲሆንልን ዳን 6:10-13, ማቴ 24:13, ማር 14:35-36, ኢሣ 26:3-4

1.10 እግዚአብሔር አምላካችንን ለማየት እንድንችል 2ኛ ዜና 16:9, ኤር 4:25, 5:1, ሕዝቅ 22:30, 2ኛ ዜና 29:1,

1.11 የከበረውን ከተዋረደው ቅዱሱን ከረከሰው ፅድቅን ከሐጥያት ለመለየት ቅጥርና ምሽግ እንዲሆንልን ኤር 15:19-21, ዳን 6:19:22, ሕዝ 44:23

1.12 በእግዚአብሔር ፊት ለሚያገለግሉት ሕዝብ መቆም ይችሉ ዘንድ ዘፀ 32:11-14, 32 ሮሜ 9:1-2, ኤፌ 3:1

2 <u>ከእግዝአብሔር ራዕይ መቀበል፣ ማግኘት አስፈላጊነቱ፣</u>

2.1 በመከራ ሁሉ ጸንተን እንድንቆም ለተገለጽልንም ራዕይ አርቀን ማየትን፣ ሰው ያላየውን እግዚአብሔር እንደሚያየው በመንፈሱ እንድንረዳው ለእግዚአብሔርም ክብር እንድንመሰክረውና እንድንናገረው ያደርገናል:: ዘፍ.37:5-11፣ 45:1-8፣ሐዋ.9:6-7፣ 26:19-20

2.2 እግዚአብሔርን ለማገልገል ከእግዚአብሔር የተሰጠን የተቀበልነው ራዕይና ፀጋ ከሌለን፣ በፈቃዳችንየምንሄድ፣ የምናገለግል ዓላማና ግብ የሌለን፣ ሥርዓት የለሽ፣ በሁኔታዎች የምንወሰድ እንሆናለን:: ምሣሌ 29:18፣ ሆሴዕ 4:6፣ 1ኛ ሣሙ.3:1

2.3 የተሰወረውንና የጠለቀውን ለማወቅ ዳን 2:22



3. <u>ራዕይ እንዴት እንቀበላለን ?</u>

3.1 እግዚአብሔር እራሱ በፍቃዱ ለክብሩና ለዓላማው ለእኛም ባርኮት የሚሰጥ ነው፡ ዘፍ. 15::1፣ 37:5-11፣ ሐዋ. 26:19-20፣ ራዕይ 1:9

3.2 በእግዚአብሔር ፊት እንደቃሉ በምንቆይበትና በምንጸልይበት ጊዜ እንቀበላለን:: ዘፀ.3:1-7፣ነህምያ 1:2-4፣ ኢሳ. 45:11፣ ሐዋ.10:3፣ 16:9-10፣ ዕንባ 2:1-3

3.3 እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በእግዚአብሔር መንፈስ በምንሆንበትና ጥበብና ማስተዋሉን፣ ትምህርቱን በምንጠማበትና በምንፈልግበት ጊዜ ራዕይን ይሰጠናል:: ዮሐ.16:13፣ ዳን.9:20-23፣ ራዕይ 1·9-20

3.4 እግዚአብሔር ራዕይን በመግለጽ ሌሎችን ከጥፋትና ከአደጋ ለማውጣትና ለማዳን ይሰጣል:: 2ኛ ሣሙ. 7:17፣ 2ኛ ነገሥ.6:8-12

3.5 የአገልግሎትን ራዕይ ከጌታ መቀበል በእግዚአብሔር ምሪትና ዕቅድ እንድንፀናና እንድንበረታ ያደርጋል:: ዘፍ. 45:1-8፣ ሐዋ.16:9-10

3.6 እግዚአብሔር ራዕይ ለተለያዩ ግለሰቦች፣ ለአንድ ሰው፣ ለሕዝብና ለአገር፣ ለአንድ ዓላማና ግብ ይሰጣል:: ዘፍ.46:2, ዳን.10:7፣ ሐዋ.9:7, 16:9-10

3.7 እግዚአብጤር ለሚሰጠን ሁሉ ፍቃዳችንን ልናደርግበት ሳይሆን ፍቃዱን እንድናደርግ ነው:: ዮሐ. 4:34

4. <u>የእግዚአብሔር የሆነ ራዕይ የሚከተሉትን ይመስላል</u>

4.1 እንድናየው ያደርጋል፣ ሉቃ.2፡25-32

4.2 እንድንሰማው ይነገራል፣ ሐዋ.10፡3, 10-11

4.3 እንድናምነው ያደርጋል፣ ዘፍ.15፡6, ሐዋ.9፡6-7

4.4 እንድንጠብቀው ያደርጋል፣ ሉቃ.24፡49, ዳን.7፡28

4.5 እንድናከብረው ያደርጋል፣ ዘፍ.41፡16, ዳንኤ 2፡27-

4.6 የሚያጠፋው የለም፣ ዘፍ?45፡1-8, ነህም 6፡15-16

4.7 ሲፈጸም ሲሆን እናየዋለን፡፡ ዘፍ.42፡7,12, ኤር .29፡10-11, ዳን.9፡2

5. <u>ከእግዚአብሔር የተሰጠን ራዕይ ሊጠፋ የሚችለው እንዴት ነው ?</u>

5.1 እንደ ይሁዳ አስቆሮቱ ጌታን በጥቅም መሰል ነገር ስንለውጠው ፣ ሉቃ.22፡3-6

5.2 እንደ ንጉሡ ሳዖል የእግዚአብሔር ቃል ንቀን የሕዝብ ድምፅ ስንሰማ፣1ኛ ሣሙ.15፡21-23

5.3 እግዚአብሔር ያለንን ብቻ አለማድረግና የሰው ሃሳብ መጨመር ያጠፋዋል፡፡ 1ኛ ነገሥ.13፡18-25

5.4 የተሰጠንን መንፈስ በቅድስና አለመጠበቅ፣ መሳእ. 16፡15-22

5.5 በራስ ምኞትና መታለል፣ መሄድ፡፡ ምሳሌ 3፡5, ገላ 6፡3



6. <u>ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ራዕይ እንዴት እንለየዋለን ?</u>

6.1 በውሸትና በጥቅም ምኞት የሚመጣ፣ ነው ኤር.14፡14, 1ኛ ነገሥ.13፡18

6.2 እግዚአብሔር ሳይሰጠን በሃሳብ በአእምሮ ሰይጣን የሚያስተላልፈውና የሚሰጠው ራዕይ ነው፣ ኤር 23፡16, ሕዝ.13፡7

6.3 እግዚአብሔር የሰጠውን ራዕይ ለማጨናገፍ፣ እንዳይከናወን በማስመሰል የሚመጣ ራዕይ ነው፣ ነሕም. 6፡12

6.4 እግዚአብሔርን የማያከብር የትዕቢትና ራስን የሚያከብር ራዕይ፣ ነው ሕዝ.28፡6-19

7. <u>እግዚአብሔር ቤቱን እንዴት በአገልጋዩ እንደሚሠራ እንወቅ</u>

7.1 ቤትን የሚሠራው እግዚአብሔር እራሱ ነው፡፡ መዝ. 127፡1

7.2 እግዚአብሔር በጽድቅ የሚታመኑትን ምሪትን ለሥራው ይሰጣል፡፡ ዘፍ. 6፡13-18, ዘፀ.25፡1-9, 2ኛ ዜና 6፡10-11

7.3 የእግዚአብሔርን ሥራ በመታዘዝ ይሠራሉ፣ ዕዝራ 1፡5, ሐጌ 1፡13-15 ዘፀ.25፡1-9, 2ኛ ዜና 6፡10-11

7.4 የእግዚአብሔርን ሥራ ያለ ጌታ ምንም ልናደርግ አንችልም፡፡ ዮሐ.15፡5

7.5 የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው በመንፈስ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፡፡ ዘካ.45-8

7.6 እግዚአብሔር ለሥራው መንፈሱን አብልጦ ይሰጣል፣ ሉቃ.11፡13, ዮሐ.3፡35

7.7 ከጌታ የተቀበልነውን አገልግሎት በቆራጥነትና ወሳኝነት ለማድረግ ከተነሳን፣ ይህን ለማድረግ ፀጋ አለው፡፡ ሐዋ. 20፡24, ቆላ.4፡17

*አሜን !!*